# እንድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 059 ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# «አህጉራችንን ጽኑ ለማድረግ በአብሮነት መሥራታችንን እንቀጥላለን»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አህጉራችንን ጽኑ ለማድረግ በአብሮነት መሥራታችንን እንቀጥላለን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በማህበራዊ ድረገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ጎን ለጎን ከወንድም የአፍሪካ አገራት መሪዎች ጋር በሁለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይተናል።

ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎችን ለመፈለግ እና አህጉራችንን ጽኑ ለማድረግ በአብሮነት መሥራታችንን እንቀጥላለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ልዑካቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔን በግብፅ፣ ሻርም አል-ሼይክ እየተሳተፉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

# የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና የሕወሓት ታጣቂዎች አዛዦች ናይሮቢ ላይ ተገናኙ

በጋዜጣው ሪፖርተር





አዲስ አበባ፡- በሰላም ስምምነቱ ወታደራዊ አመራሮች በ5 ቀናት ውስጥ እንዲገናኙ በተቀመጠው መሠረት የአዛዦቹ ውይይት ትናንት በናይሮቢ ተጀምሯል።

የአዛዦቹ ውይይት ትናንት በኬንያ ናይሮቢ ከተማ መጀመሩን የሰላም አማራጭ አብይ ኮሚቴ አባል እና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገልጸዋል።

የአፍሪካ ህብረት (AU) ባወጣው መግለጫ ሁለቱ የጦር አመራሮች በደቡብ አፍሪካ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት ምክክር መጀመራቸውን ገልጿል።

ትናንት የጀመረው ውይይት በትግራይ አስቸኳይ የሰብአዊ ድጋፍ መስመር ተከፍቶ የተቋረጡ አገልግሎቶች እንዲጀምሩና ታጣቂዎች ትጥቅ በሚፈቱበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ እንደሚሆን ይጠበቃል።

የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንትና የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ ቀደም ሲል የሰላም ውይይቱን በተመለከተ እንደተናገሩት፤ በደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የሰላም ስምምነት ግጭትን በማስቆም ለዘላቂ ሰላም መስፈን አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው። ስምምነቱም ችግሮችን በዘላቂነት በውይይት እንዲፈቱ የሚያስችል በመሆኑ ሁሉም አካላት ለተፈጻሚነቱ በጥበብና አገር ወዳድነት ስሜት በጋራ ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

በአፍሪካ ህብረት አማካኝነት በደቡብ አፍሪካ በኢፌዴሪ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል ሲካሔድ የቆየው የሰላም ውይይት የኢትዮጵያ ሕዝቦችን የጋራ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መጠናቀቁ ይታወሳል።

ስምምነቱ በአንድ ሉዓላዊ አገር ውስጥ ሁለት የታጠቀ


የኢትዮጵያ መከላከያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

pepsi




# የአርቲስት አሊ ቢራ ሥርዓተ ቀብር ዛሬ ይፈጸማል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በሙዚቃ ሥራው ለስድስት አስርት አመታት ለፍትሕና ለነፃነት የታገለውና ያታገለው የክብር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ ሥርዓተ ቀብር ዛሬ በድሬዳዋ እንደሚፈፀም ለሽኝት መርሃግብር የተቋቋመው አብይ ኮሚቴ አስታወቀ።

የአርቲስት አሊ ቢራን የቀብርና የሽኝት ሥነ


የአርቲስት አሊ ቢራ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# «የሠላም ስምምነቱ አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ የሚያረጋግጥ ነው»

- ዶክተር አረጋዊ በርሄ
የት.ዴ.ፓ ሊቀመንበር

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሠላም ስምምነት አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ ትልቅ መልዕክት ያስተላለፈ ታሪካዊ ስምምነት መሆኑን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) ሊቀመንበር ዶክተር አረጋዊ በርሄ አስታወቁ። ለስምምነቱ እውን


«የሠላም ስምምነቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









የሰላም ስምምነቱ አፈፃፀም የሁሉንም ትብብር ይጠይቃል


ገጽ 3

ዜና



# ከ360 በላይ የማዕድን ኩባንያዎች የሚሳተፉበት ኤክስፖ ሊካሄድ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ከ360 በላይ የአገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት «ማይንቴክስ» የተሰኘ ዓለምአቀፍ የማዕድን ኤክስፖ በኢትዮጵያ እንደሚካሄድ የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ። ኤክስፖው ከኅዳር አንድ እስከ ሦስት በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳልም ተብሏል።

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫቸው እንዳሳወቁት፤ በ«ማይንቴክስ» ዓለምአቀፍ የማዕድን ኤክስፖ ላይ ከ360 በላይ የማዕድን ኩባንያዎች ይሳተፋሉ።

ኢንጂነር ታከለ በገለፃቸው፤ ዓለምአቀፍ የማዕድን ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት በማስተዋወቅ ኩባንያዎች በቴክኖሎጂ በመታገዝና ፋይናንስ በመመደብ ዘርፉን እንዲያግዙ የሚያስችልና በዘርፉ ያሉ ተዋንያንን በቴክኖሎጂ እንዲሁም በፋይናንስ የሚያስተሳስር ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ተስፋ የሚጣልባትና በዘርፉ አሉ ከሚባሉ አገሮች ተርታ የምትመደብ ናት ያሉት ኢንጂነር ታከለ፤ የኤክስፖውም ዋና አላማ ይህን ሀብትና ፍላጎት ማሳወቅ ነው ብለዋል።

ኤክስፖው አምራቾችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ገዢዎች ጋር በቀጥታ ያገናኛል ያሉት ኢንጂነር ታከለ በኤክስፖውም የአገር ውስጥና የውጭ የማዕድን ኩባንያዎች፣ የጌጣጌጥ አምራቾችና ላኪዎች፣ የማዕድን ቴክኖሎጂ አምራቾችና አስመጪዎች እና የፋይናንስ ተቋማት እንደሚሳተፉ ገልጸዋል።

ከውጭ የሚመጡ የማዕድን ኩባንያዎች በኤክስፖው ላይ መሳተፋቸው በአገራችን ያለውን የማዕድን ኢንቨስትመንት አማራጭ እንዲመለከቱና የማዕድን ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፉ ዕድል እንደሚፈጥርም ነው ኢንጂነር ታከለ የተናገሩት።

በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለ ሀብቶች ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የገበያ ትስስር ይፈጥሩበታል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በኤክስፖው በአገር ውስጥ የሚገኙ 270 እንዲሁም ከ90 በላይ የውጭ ኩባንያዎች ይሳተፋሉ ሲሉም ገልጸዋል።

በኤክስፖው የኢትዮጵያ የማዕድን እምቅ ሀብት የአሁን ገፅታ እና የወደፊት ተስፋ ይገለፃል ተብሎ እንደሚጠበቅ የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ በዚህ ኤክስፖ የማዕድን ቴክኖሎጂ አምራቾች መሳተፋቸው ለአገራችን የማዕድን ዘርፍ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለመተዋወቅ እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

ከውጭ የሚመጡ የማዕድን ኩባንያዎች በኤክስፖው ላይ መሳተፋቸው በአገራችን ያለውን የማዕድን የኢንቨስትመንት አማራጭ እንዲመለከቱና በዘርፉ መዋዕለ-ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ዕድል ይሰጣል ያሉት ኢንጂነር ታከለ፤ በዚህም አገልግሎታቸውን በቀጥታ ለአገር ውስጥና ለውጭ ሸማቾች እንደሚያስተዋውቁ ገልጸዋል።

በማዕድን ዘርፉ ላይ ትኩረት ያደረጉ የቴክኖሎጂ አምራቾች መሳተፋቸውም የአገራችን የማዕድን ዘርፍ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን እንዲተዋወቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል ሲሉም አክለዋል።

ዓለም አቀፍ የማዕድን እና ቴክኖሎጂ ኤክስፖው "Mintex" ከሐሙስ ኅዳር አንድ ቀን እስከ ኅዳር ሦስት ቀን 2015 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የሚካሄድ ሲሆን በመጪው ሐሙስ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በዘርፉ የተሰማሩ አምራችና ሻጭ ኩባንያዎች በተገኙበት ይከፈታል።

# ለመንግሥት የጤና ተቋማት የመድኃኒት ግዥ በየዓመቱ 15 ቢሊዮን ብር ወጪ ይደረጋል

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ለመንግሥት የጤና ተቋማት የመድኃኒት ግዥ በየዓመቱ 15 ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሚደረግ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አስታወቀ።

በጤና ተቋማት የሚቀርቡ የመድኃኒት ጥያቄዎች በጥናት ላይ ያልተመሠረቱና ትክክለኛ የፍላጎት መጠንን የሚገልጹ ባለመሆናቸው አንዳንዶች ላይ እጥረት ሲከሰት ያለፍላጎት በብዛት ወደ ገበያው የሚቀርቡም እንዳሉና አገልግሎቱ ለመንግሥት የጤና ተቋማት የመድኃኒት ግዥ በየዓመቱ 15 ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሚያደርግም የአገልግሎቱ የኮሚዩኒኬሽን ክፍል ገልጿል።

ከ5 ሺህ ለሚበልጡ የጤና ተቋማት በየዓመቱ ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ መድኃኒቶች እና የሕክምና ግብዓቶች እንደሚያቀርብ የአገልግሎቱ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት 85 በመቶ የሚሆነውን መድኃኒት በማስገባት 15 ከመቶ የሚሆኑትን በራሷ አምርታ የምታቀርባቸው የመድኃኒት ዓይነቶች ብዛት 348 ቢሆኑም ይህንን አሠራር ለማሻሻል እቅድ አውጥታ እየተንቀሳቀሰች እንደምትገኝ ነው የተጠቆመው።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የመድኃኒት ግዢ የሚፈጽምባቸው ቀዳሚ አገራት ሕንድ፣ ሲፕረስ እና ቻይና እንደሆኑ የገለጹት ዳይሬክተሩ፣ ከሌሎችም አገራት በተወሰነ ደረጃ የመድኃኒት ግዢ እንደሚፈጸም ተገልጿል።

መድኃኒቶችን ማቅረብና ማሰራጨት ብቻ የአገሪቷን የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን ይፈታል ባይባልም የተሰራጩትን መድኃኒቶች በአግባቡ አገልግሎት ላይ ውሏል ወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሥርዓት ማበጀት እንደሚገባ ነው የተገለጸው።

የጤና ተቋማት በጥናት ላይ በተመሠረተና በትክክለኛ ፍላጎታቸው ልክ የመድኃኒት ግብዓቶችን ወስደው ለኅብረተሰቡ በአግባቡ ተደራሽ በማድረግ የመድኃኒት አቅርቦትና ፍላጎትን ማጣጣም እንደሚገባ ተገልጿል።

ይህ ካልሆነ ግን የመድኃኒት ብክነትና እጥረትን ከማስከተሉም ባለፈ ማህበረሰቡ ማግኘት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በአግባቡ ሳያገኝ ይቀራል ተብሏል።

የዓለም አቀፍ መድኃኒት አቅራቢዎች ብዛት 185 ቢሆንም አሁንም በአገሪቱ ያለውን የመድኃኒት አቅርቦትና ፍላጎት ማጣጣም እንዳልተቻለ መገለጹን የዘገበው ኢቢሲ ነው።

# የሰላም ስምምነቱ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያን አሸናፊ ያደረገ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተደረገው የሰላም ስምምነት የዜጎችን ዘላቂ ሰላም በማስጠበቅ በጋራ ለመበልጸግ የሚያስችለንን መሠረት የጣለ መሆኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰላም ስምምነቱ የታለመለትን ዘላቂ ሰላም እንዲያመጣ ለተግባራዊነቱ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለመወጣት ከወዲሁ ዝግጁ መሆኑንም አስታውቋል።

የክልሉ መንግሥት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የክልሉ መንግሥት ቅድመ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በትግራይ ክልልና በአማራ ክልል ሕዝብ መካከል ለክፍለ-ዘመናት የዘለቀው የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ባህላዊና መንፈሳዊ ትስስር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለሰላም እጁን ዘርግቶ ሲጠባበቅ መኖሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ መሆኑን አስታውሷል።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተደረገው የሰላም ስምምነት ለሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች ዳግም ትንሳኤ ወሳኝ ከመሆኑም በላይ ከቂምና ከቁርሾ የዘለለ ህብረትን፣ አንድነትንና የጋራ እሴትን በጋራ የምንገነባበትን መሠረት ይጥላል ብለን እናምናለን ብሏል ክልሉ በመግለጫው።

የደቡብ አፍሪካው የሰላም ስምምነት እውን በመሆኑ የተሰማንን ደስታ እየገለጽን ለተግባራዊነቱ የሚጠበቅብንን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን



አበክረን እንገልፃለን ሲልም አረጋግጧል።

ስለሆነም በጦርነቱ ምክንያት የወደመውን የሕዝብ ሀብት መልሶ ለመተካትና የዘላቂ መልሶ ግንባታ ሥራው እንዲፋጠን ለማድረግ ከምንጊዜውም በላይ እንደ ሕዝብ የተፈጠረውን የሰላም አየር ተጠቅመን መረባረብ ይኖርብናል ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

ሰላም ወዳድ የሆነው የክልሉ ሕዝብም የሰላም ስምምነቱ ለአገር ሉዓላዊነትና ለግዛት አንድነት ወሳኝ መሆኑን በመረዳት ከደረሰብን ጉዳት ለማገገምና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት እንደወትሮው ሁሉ ከክልሉ መንግሥት ጎን በመቆም አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርቧል።



# ክልሉ በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ክልል በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም ድጋፍ እንደሚያደርግ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው ገለጹ።

አቶ ርስቱ ይርዳው የክልሉ የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸም ትናንት በሀዋሳ ከተማ በተገመገመበት ወቅት እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ በጦርነቱ ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ይደግፋል።

በሌላ በኩል በሰላም ስምምነቱ ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆናለች ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ሁሉም ዜጋ በተቀናጀ መንገድ የተጣለበትን ኃላፊነት እንዲወጣም ጥሪ አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ በጦርነቱ ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት የክልሉ መንግሥት እንደሚደግፍም ተናግረዋል።

በሌላ በኩልም በክልሉ ባለፉት ሦስት ወራት የተከናወኑ ተግባራትን በመፈተሽ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋትና ድክመቶችን በመለየት ለላቀ አፈጻጸም መሥራት እንደሚገባ አመልክተው፤ የክልሉ አመራሮች እና ሠራተኞች በውጤት ላይ የተመሠረተ አፈጻጸም እንዲያስመዘግቡም አሳስበዋል።

ለሁለት ቀናት በሚቆየው መድረክ ላይ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እየተሳተፉ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

# አርቲስት አሊ ቢራ - ታላቁ የአፍሪካ የጥበብ ዋርካ

**ዳግማዊት ግርማ**



የኢትዮጵያ ለምለም ማህጸን የሙዚቃ ጥሟን ለማርካት የሚያስችሏትን ልጆች ለመውለድ ቦዝኖ አያውቅም። ከወጣት እስከ አንጋፋ ከያኒያን ልጆች እናት ናት። ከመልካም ልጆቿ መካከልም አሊ መሐመድ ስሙ በቀዳሚነት ይነሳል።

አሊ በግንቦት 1940 ዓ.ም የሰላም፣ የፍቅርና የመዋደድ ተምሳሌት በሆነችው ድሬዳዋ ከተማ ተወለደ። አርቲስቱ ምድር ላይ ከቆየባቸው 75 አመታት ከ50 ዓመታት በላዩን ለሙዚቃ ለግሷል።

ቤተሰቦቹ የሚያውቁት ስሙ አሊ መሐመድ ሲሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አሊ ቢራ በሚለው የመድረክ ስሙ ያውቀዋል። በነዚሁ ከግማሽ ክፍለዘመን ለሚልቁ አመታትም በሙዚቃ እንደነገሰ ከርሟል። «ቢራ» የሚለው የኦሮምኛ ቃል የተወሰደው አሊ ለመጀመሪያ ጊዜ መድረክ ላይ ካቀረበው ዘፈን፣ «ቢራ ዳ ባሬ» ነው። እንደ ቀልድም አሊ ቢራ የሚለው ስሙ ሆኖ ቀረ።

አርቲስት አሊ ቢራ ዜማን ይቀምር፣ ግጥምን ይደርስ፣ ሙዚቃን ያቀናብር እንደነበረ ለማወቅ ትንሽ ስለ ሙዚቃ ማወቅ በቂ ነው፤ በአሊ ዘፈኖች ለመቦረቅ እንዲሁም በስንኞቹ ለማዘን ኦሮሞ መሆን ወይ ኦሮምኛን ማወቅ አያሻም፤ ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ ነውና በዘፈኖቹ ለመደሰት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው።

አርቲስት አሊ ከኦሮምኛ በተጨማሪ፣ በሶማሊኛ፣ በአፋርኛ፡ በሐረሪ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች አቀንቅኗል። ከ267 በላይ ሙዚቃዎችንም ተጫውቷል። የዘፈኖቹ ድንቅ መልዕክትም የልጅነታችን የዋህነት፣ የወጣትነታችን ሩጫ፣ የእርጅናችን ምርኩዝ ሆነው ይኖራሉ። ሙዚቃም ያለ ድካም ከሃምሳ ለሚልቁ አመታት እንዳላት ስትሆንለት ኖራለች።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በድሬዳዋ ከተማ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በአዲስ አበባ ካቴድራል ትምህርት ቤት ተከታትሏል። እንዲሁም አሜሪካ አገር በሚገኘው የሳንታ ሞኒካ ኮሌጅም የሙዚቃ ትምህርቱን ተምሯል።

አርቲስት አሊ ቢራ ከሙዚቃ ጋር የቆየ ትውውቅ ቢኖረውም በኢትዮጵያውያኑ የጊዜ ቀመር 1954 ዓ.ም «አፍረንቀሎ» የተሰኘ የባህላዊ ሙዚቃ ቡድንን በመቀላቀል ከሙዚቃ ጋር ሕጋዊ ጋብቻውን ፈጸመ።

በክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ ተቀጥሮ ለሦስት ዓመታት እንዲሁም 'አይቤክስ' ባንድን በመቀላቀል በዲ አፍሪክ ለስምንት ዓመታት የሙዚቃ ሥራዎቹን አቅርቧል። አሊ ጊታር፣ ፒያኖ፣ ኡድ እና ሌሎች የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይጫወታል። ከአርባ በላይ አገራት በርካታ በሆኑ መድረኮች የሙዚቃ ሥራዎችን ተጫውቷል።

በኪነጥበቡ ዘርፍ ላበረከተው አስተዋፅኦ እልፍ ሽልማቶችንና የክብር ዶክተሬት ማዕረግም የተሰጠው አርቲስት አሊ ቢራ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ተቋማት የተለያዩ እውቅናዎችን እና ሽልማቶችን አግኝቷል።

አንጋፋው ሁለገቡ አርቲስት አሊ ቢራ ባጋጠመው የጤና እክል ምክንያት በአዳማ ጄነራል ሆስፒታል ለሳምንታት የሕክምና ክትትል ሲደረግለት ቆይቶ ከትናንት በስቲያ አመሻሽ ላይ በ75 ዓመቱ አርፏል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በ75 ዓመቱ ይቺን ምድር የተሰናበተውን፣ የቋንቋን ድንበር መሻገር የቻለውን አሊን ህልፈተ ሕይወት በሚመለከት የሙያ አጋሮቹ የተሰማቸውን ኀዘን ይገልፁ ዘንድ ዕድል ሰጥቷል። የሙያ አጋሮቹም ድምፃዊ አሊ ኩራትን የማያውቅ ሁሉንም በእኩል የሚመለከት ሰው ነበር ሲሉ መስክረውለታል።

አስተያየቱን ለድርጅታችን የሰጠው ድምፃዊ ጌቴ አንለይ እንደተናገረው ከምድር ሲለዩን በሕይወት ሲያልፉ እንደሚወራላቸው ሰዎች ሳይሆን አሊ ከልቡ መልካም ሰው ነበር፤ ኩራትን የማያውቅ፣ ሁሉንም በእኩል የሚመለከት ሰውም ነበር።

ድምፃዊ ጌቴ በምስክርነቱ እንደገለጸው፤ አርቲስት አሊ በዘመናት መካከል ደግሞ ሊፈጠር የማይችል ድንቅ ድምፅ ባለቤት ነው፤ ትሁትና ሰውን የሚወድ ማንኛውም ሰው ትንሽ ነገር ሲሰራ ገርሞት ሰውን አድንቆ የሚያበረታታ ነው።

ለድምፃዊ ጌቴ አርቲስት አሊ የገራሚ ድምጽ ባለቤትና ድምጹም ለማስመሰል የሚከብድ ነው። እንደ አሊ ያሉ አንጋፋ የጥበብ ሰዎችን በሕይወት እያሉ ለአገራቸው የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ከእግራቸው ስር ሆኖ እውቀታቸውን መቅሰም ያስፈልጋል።

የኦሮሚኛ ሙዚቃ አቀንቃኙ ደመረ ለገሰ በበኩሉ ድምፃዊ አሊ አገርን ተሻግሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያገኘ አርቲስት ነው። ሞት ተፈጥሯዊ ነው፤ እንደአሊ ብዙ ሠርቶ መሞት ግን መታደል ነው ብሏል።

ድምፃዊ አሊ ያስጀመራቸውን የጥበብ ሥራዎች መጪው ትውልድ የሙያ ሥነምግባሩን በመጠበቅ ሊያስፈፅም እንደሚገባም ድምፃዊ ደመረ ገልጿል።

ድምፃዊ ደመረ ለድምፃዊው ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመዶች፣ ለሙዚቃ አፍቃሪያን እንዲሁም ለጥበብ ሰዎች መፅናናትን ተመኝቷል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኛና አመራሮችም በሙዚቃው ንጉሥ ሞት የተሰማንን ጥልቅ ኀዘን እንገልፃለን።

# የሠላም ስምምነቱ ለቱሪዝሙ ዘርፍ ትንሳዔ ነው

**አዲሱ ገረመው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በኢትዮጵያ የሰሜኑን ግጭት ለማቆም የተደረገው የሠላም ስምምነት ለቱሪዝሙ ዘርፍ ትንሳዔ መሆኑ ተገለጸ። በ2015ዓ.ም የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከውጭ ቱሪስት አንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር የ2015በጀት ዓመት እቅድና የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም ትናንት ለንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል። በመድረኩ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ፤ በዘንድሮ ዓመት ቱሪዝሙን ለማነቃቃት የተሻለ ዕድል መኖሩን ገልጸዋል። ምንም ነገር ቢከናወን ሠላምና ጸጥታ በሌለበት ስለ ቱሪዝም ማሰብ አይቻልም በማለት፤ አሁን ላይ የተፈጠረው የሠላም ስምምነት ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስታውቀዋል። ዘርፉን የበለጠ ለማነቃነቅ ሰፋፊ የገጽታ ግንባታና የማስተዋወቅ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው ብለዋል።

አገሪቱ ውስጥ በተፈጠረው የሰላም ሥምምነት በርካታ የቱሪስት ፍሰቱ እንደሚኖር፤ ቱሪስት ላኪ የሆኑ ድርጅቶችም ሠላሙን በመተማመን ቱሪስት እንደሚልኩ ጠቅሰዋል። በሆቴልና ኢንቨስትመንት ረገድም መሠማራት የሚፈልጉ የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስት እንደሚያደርጉና ለዚህም የሠላም ስምምነቱ ለቱሪዝም ዘርፉ እንደ ትንሳዔ እንደሚታይ አቶ ስለሺ ተናግረዋል።

በ2015 የበጀት ዓመት ከአስር ዓመቱ መሪ እቅድ ጋር የተጣጣሙ ተግባራትን ለማከናወን ሚኒስቴሩ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ በዓመቱ የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ፣ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራዎችን ማሳደግ፣ የቱሪዝም መዳረሻና መስህብ ልማት ሥራዎችን ማጎልበት፣ ለሆቴሎች የኮከብ ደረጃ እውቅና መስጠት፣ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን መገንባት፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ሙዚየም ግንባታን የማከናወን ሥራዎች በትኩረት እንደሚሠሩ ገልጸዋል።



ፎቶ - በሃይሽ አብርሃ

**አቶ ስለሺ ግርማ**

በሩብ የበጀት ዓመት በነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እሴቶችን የመጨመር ሥራ መከናወኑንም አቶ ስለሺ ጠቁመዋል። ተዘግተው የነበሩ የቱሪስት መዳረሻዎች መከፈታቸውንና አዳዲስ የቱሪዝም ምርቶች መተዋወቃቸውን ገልጸዋል። ዘርፉን የበለጠ ለማነቃቃት በተሠራ ሥራ 38 አዳዲስ ባለሀብቶች የቱሪዝም ኢቨንስትመንቱን መቀላቀል እንደቻሉም አስታውቀዋል።

በሩብ ዓመቱ 350 ሺህ የውጭ ቱሪስት ፍሰት ለማድረስና ከዚህም አንድ ነጥብ 39 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ፤ 260 ሺህ የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች በኢትዮጵያ ጉብኝት ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል። ከዚህም ወደ አንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ 17 ሚሊዮን የአገር ውስጥ ቱሪስት እንቅስቃሴ እንደነበርና 14 ቢሊዮን ብር ተንቀሳቅሷል ሲሉ ጠቅሰዋል። በዚህም ከተሞችና የቱሪዝም መዳረሻ ያለባቸው አካባቢዎች መነቃቃታቸውን ተናግረዋል። የሥራ ዕድሉም እያደገ ነው ብለዋል። በቱሪዝሙ ሴክተር 14 ሺህ ዜጎች በሩብ ዓመቱ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸውም አቶ ስለሺ ጠቅሰዋል። የቱሪስት ቆይታ ጊዜ ወደ 17 ቀናት እንዲያድግ መደረጉንም ገልጸዋል።

# «የሰላም ስምምነቱ ለአገር አንድነትና ለሕዝቦች ወንድማማችነት ገንቢ ሚና ይጫወታል»

\- ኦነግ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በደቡብ አፍሪካ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ለአገር አንድነትና ለሕዝቦች ወንድማማችነት ገንቢ ሚና እንደሚጫወት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር(ኦነግ) አስታወቀ።

ኦነግ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንደገለጸው፣ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ከተፈጸመው ጥቃት ጋር ተያይዞ በአገሪቱ የተደረገው ጦርነት በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ አስከፊ ውድመት አድርሷል።

ባለንበት ክፍለ ዘመን በጠብመንጃ አፈሙዝ የሚፈታ ችግር አይኖርም ያለው መግለጫው፤ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ የበላይነት በኃይልና ጠብ መንጃ እንደማይረጋገጥ ለተከሰቱትና ለሚከሰቱ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በመወያየት መፍታት ብቸኛው መንገድ ነው ብሏል። ከዚህ ውጪ የሚመረጠው መንገድ ያየነውን ውድመት ከማስከተል ባለፈ የሚያስገኘው መፍትሄ የለም ሲልም ጠቁሟል።

በጦርነቱ በሕፃናት፡ በአዛውንቶችና በወጣቶች ላይ ያደረሰው ጥፋትና በንብረት ላይ የደረሰው ውድመት ሲታይ አሳዛኝና የሚያስቆጭ መሆኑንም አስገንዝቧል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካ ሕብረት መፈታት አለበት በማለት ያሳየው ጽኑ አቋም አፍሪካንና ኢትዮጵያን እንዳስከበረም መግለጫው አትቷል።

የሰላም ስምምነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም ከአርባ ዓመታት በላይ ሙብቱንና ነፃነቱን ተገፎ በአፈና ስር ሲማቅቅ ለነበረው ለትግራይ ሕዝብ ነፃነቱን የሚያጎናጽፍና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፍ የመጣውን እልቂትና ድህነት የሚያቆም መሆኑንም ጠቁሟል።

እንደ መግለጫው፣ ስምምነቱ በአንድ አገር ውስጥ ባሉ ዜጎች መካከል የሚታየውን የደም መፋሰስ በማቆም በዕድገትና ልማት ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ፣ ጥላቻን በፍቅር የሚተካ፣ ከጠላትነት ወንድማማችነትን ለማጎልበት ዕድል የሚሰጥ ነው። ያም ሆኖ ግን ተግባራዊ እንዲሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይጠይቃል።

በተካሄደው ወረራ አገርና ሕዝብ ተጎድተዋል ያለው የኦነግ መግለጫ፤ የወደመውን መልሶ የመገንባት ሸክም የሕዝብና የመንግሥት መሆኑን በመረዳትና ከደረሰው ውድመት በመማር መሰል ጥፋት እንዳይከሰት ሰላም የማስከበር ሂደት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት እንዲሆን ጠይቋል።

# ከ 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ የወባ መከላከያ አጎበር ተሰራጨ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ የሚከሰት የወባ በሽታን ለመከላከል በመጀመሪያው ዙር በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን የወባ መከላከያ አጎበር ማሰራጨቱን አስታወቀ።

የአገልግሎቱ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ አወል ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አገልግሎቱ በአንድ ወር ጊዜ አጎበሮችን ለማሰራጨት እቅድ ይዞ ባሣለፍነው ሣምንት በመጀመሪያው ዙር በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን አጎበሮችን አሰራጭቷል።

ለወባ ተጋላጭ በሆኑባቸው አካባቢዎች 16 ነጥብ 7 ሚሊዮን አጎበሮችን ለማሰራጨት መታቀዱን የተናገሩት አቶ አወል፤ በዚህም በመጀመሪያው ዙር 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን አጎበሮች የተሰራጨ ሲሆን፣ የተቀሩት እስከ የካቲት ወር ድረስ እንደሚሰራጭም አመልክተዋል።

የአጎበር ስርጭቱን በ11 የአገልግሎቱ ቅርንጫፎች አማካኝነት ማለትም ነቀምት፣ ጅማ፣ ነገሌ ቦረና፣ ድሬዳዋ፣ አዳማ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ሐዋሣ፣ አርባ ምንጭ እና በአዲስ አበባ እንደሚከናወን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ አጎበሮቹ በገንዘብ ሲተመኑ ወደ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ወጪ ተደርጎባቸዋል ብለዋል።

አጎበሩ የወባ ትንኝ የምታስተላልፈውን የወባ በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው ያሉት አቶ አወል፤ ለወባ ተጋላጭ በሆኑባቸው አካባቢዎች የወባ በሽታ አስቀድሞ ለመከላከልና



ለመቆጣጠር እንደሚያስችል ተናግረዋል።

እንደ አቶ አወል ገለፃ፤ የወባ በሽታ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገራት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በዕድሜም ሆነ በፆታ ሳይለይ የሚያጠቃ ዋነኛ የጤና እና የማህበራዊ ዕድገት ችግር ነው። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ መልከዓ ምድር 75 በመቶ የሚሆነው ለወባ በሽታ ስርጭት አመቺ በመሆኑ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው 52 በመቶ ሕዝብም ለበሽታው ተጋላጭ ነው።

በሽታው በአብዛኛው የሚከሰተው ዋናውን የክረምት ዝናብ ተከትሎ በመኸር ወይም በምርት መሰብሰቢያ ወቅት በመሆኑ አስቀድሞ በሽታውን ለመከላከል ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣዩ ክረምት የወባ ትንኝ ቁጥጥር ሥራዎችን ለማጠናከር የሚያስችል ግብዓቶችን ለማሟላት ተቋሙ ከምን ጊዜውም በላይ እየሠራ ነው ብለዋል።

በልማት ኮሪደሮች የወባ በሽታ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የልማት ቀጣና ባላቸው የተመረጡ አካባቢዎች ጊዜያዊ የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን መቋቋማቸውንም ዳይሬክተሩ አክለው ገልጸዋል።

# የሰላም ስምምነቱ አፈፃፀም የሁሉንም ትብብር ይጠይቃል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራል መንግሥት እና ሕወሓት መካከል የተደረሰውን ስምምነት ወደ መሬት አውርዶ ተግባራዊ ለማድረግ የሁሉም ማኅበረሰብ ትብብር ወሳኝ መሆኑን አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ተናገረ። አትሌት ኃይሌ በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በሁለቱ አካላት መካከል በተከወነው የሰላም ስምምነት የተሰማውን ጥልቅ ደስታም ገልጿል።

አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፀው፣ የሰላም ስምምነቱ መልካም ቢሆንም ተግባራዊነቱ ግን ከፍተኛ ትዕግስትና ፅናትን የሚጠይቅ በመሆኑ የሁሉንም ማኅበረሰብ ትብብር ይጠይቃል።

የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራዎች መከወን እንደሚገባቸው ያመላከተው አትሌት ኃይሌ፤ ስምምነቱን የተፈራረሙት መንግሥትና ሕወሓት ብቻ ሳይሆኑ ከባለድርሻ አካላትም ብዙ እንደሚጠበቅ ነው የገለፀው።

ላለፉት ሁለት አመታት በጦርነቱ ምክንያት ያለ ትምህርት የቀሩ ሕፃናት ያለ ሕክምና ማዕከል በመውለድ ሕይወታቸውን ያጡ እናቶችና ሌሎችም ሰዎች የመከራው ገፈት ቀማሽ መሆናቸውን ያወሳው አትሌት ኃይሌ፤ የሰላም ስምምነቱም ከዚህ በኋላ ላለው ሞትና ጥፋት መዳኛ ይሆናል የሚል እምነት እንዳለው ነው የተናገረው።

በእርቅ ጊዜ መተው ማለት ይቅር ብያለሁ ከሚል መንፈስ የሚመጣ ነው ያለው አትሌት ኃይሌ፤ በሰላም ስምምነቱ አሸናፊም ተሸናፊም የለም፤ ሁለቱም ቡድኖች እኔ አሸንፌያለሁ የሚል ስሜት ሊሰማቸው አይገባም፤ ከሰላሙ ኢትዮጵያ አሸንፋለች ብሏል።

የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዲሆን በአጋደሉት ልክ የሚከፈላቸውን አክቲቪስቶች አናዳምጣችሁም ልንል ይገባል ያለው አትሌት ኃይሌ በተደላደለ ስፍራ ተቀምጦ የሚበላው የሌለውን የደሀ ልጅ እንዳይስማማ የሚያደርጉ ተከፋይ አክቲቪስቶችን በቃ ማለት እንደሚያስፈልግም ገልጿል።

የአማራ፣ ትግራይ፣ የአፋር እንዲሁም የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ የጥይት ድምጽ መስማት እንደማይሻ የገለጸው አትሌት ኃይሌ በውጭ አገራት የሚኖሩ አክቲቪስት ነን ባዮችን አለማድመጥ ስምምነቱ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል መሆኑንም አስረድቷል።

አንድም የጥይት ጩኸት ከማያዳምጡበት ስፍራ ተቀምጠው «በለው፣ ፍለጠው፣ ግፋ በለው፣ የምን ድርድር ነው፤ ወዘተ» እያሉ የጦርነት ጎሳሚዎችንና የራሳቸውን መደላድል አስቀምጠው የራሳቸውን እንጀራ እያበሰሉ ምስኪኑን ሕዝብ የሚያባሉትን ማድመጥ አይገባም ብሏል።

አትሌት ኃይሌ በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት ዘግይቶም ቢሆን በተከወነው የሰላም ስምምነት የተሰማውን ጥልቅ ደስታም ገልጿል።

በአፍሪካ ኅብረት አማካኝነት በደቡብ አፍሪካ በኢፌዴሪ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል ሲካሔድ የቆየው ውይይት የመላ ኢትዮጵያ ሕዝቦችን የጋራ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መጠናቀቁ ይታወሳል።

## የኢትዮጵያ መከላከያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃይል ሊኖር እንደማይችል ያስቀመጠ ሲሆን፣ የሕወሓት ታጣቂዎችም ትጥቅ እንደሚፈቱና ይህን ለማስፈጸም የሁለቱ ወገኖች የጦር መሪዎች ተገናኝተው በዝርዝር አፈጻጸሙ ላይ እንደሚወያዩ አስፍሯል።

በትግራይ ክልል መሠረታዊ አገልግሎት እንዲጀመርም ከስምምነት ላይ ተደርሷል። የኮሚቴው አባልና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ሰሞኑን ለከፍተኛ ባለስልጣናት ገለጻ ሲያደርጉ እንዳሉት፤ ስምምነቱ በዋናነት የኢትዮጵያን ዘላቂ ሰላም፣ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ማስጠበቅ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በዚህም ስምምነቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን የጋራ ጥቅም ባስከበረ መልኩ መጠናቀቁን ነው የተናገሩት።

በአንድ ሉዓላዊ አገር ውስጥ ሁለት የታጠቀ ኃይል ሊኖር እንደማይችልና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበር እንደሚገባ ስምምነት ላይ ተደርሷል ነው ያሉት።

ከዚህ አኳያ ከሕገ-መንግሥት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ቆመው በትግራይ ክልል በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ጊዜያዊ አስተዳደር እንደሚቋቋምም ተናግረዋል።

ያለን አማራጭ እና መፍትሄ በጋራ ተሳስሮ መሄድ ነው ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፤ ከዚህ አኳያ ጉዳት የደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከጉዳታቸው አገግመው ወደ ቀደመው ማህበራዊ ትስስር እንዲመለሱ በጋራ ይሠራል ነው ያሉት።

የደረሰው ጉዳት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ የወደሙ ተቋማትን ጨምሮ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች በጋራ ርብርብ ሊከናወኑ ይገባል ብለዋል።

የትስስርና የተግባቦት ሥራዎችም የሕዝቦችን መጻኢ የጋራ ጉዞ ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ እንደሚገባም አንስተዋል።

በተለይ የመገናኛ ብዙኃን ቁርሾዎችን ማባባስ ሳይሆን ዜጎች ከችግሩ ተምረው በቀጣይ አብሮነታቸውን አጠናክረው የሚሄዱበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ድሉ ለኢትዮጵያ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ወደፊት መጓዝ እንጂ ያለፈውን ቁስል ማሰላሰል አይገባም ሲሉም ነው የገለጹት።

በደቡብ አፍሪካ የተፈረመው ስምምነት በኢትዮጵያ የዛሬ አራት ዓመት ገደማ የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ ለማሳለጥ የሚያስችል መሠረት የጣለ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም መግለጻቸው ይታወሳል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስምምነቱን አስመልክተው በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢትዮጵያ ለሰላም ያላት ቁርጠኝነት አሁንም የፀና ነው። ስምምነቱ ወደ ተግባር እንዲለወጥም አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ ጠንካራ አቋም አለን ብለዋል።

## «የሠላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆን ሁሉም ኃላፊነቱን እንዲወጣም አሳስበዋል።

የፓርቲው ሊቀመንበር ዶክተር አረጋዊ በረሄ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በፌዴራል መንግሥቱና በሕወሓት መካከል የተደረገው ስምምነት ለሁሉም እፎይታ የሚሰጥና እንደ አፍሪካ አህጉር ትልቅ መልዕክት ያስተላለፈ ታሪካዊ ስምምነት ነው። ስምምነቱም በፍጥነት ወደ ተግባር ተቀይሮ ሊታይ ይገባል ብለዋል።

ትዴፓ ከዚህ በፊትም «ሠላማዊ መንገድ ያዋጣል፣ ጦርነት አያዋጣም» በማለት ሃሳብ ሲያቀርብ እንደነበረ አስታውሰው አሁንም የተጀመረው የሠላም ስምምነት ስቃይ ላይ ለነበረው ሕዝብ ትልቅ እፎታ በመሆኑ በበጎ መመልከታቸውን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ገለጻ፤ በሁሉም ክልሎች በጦርነቱ ለተሰቃዩ ሕዝቦች የሠላም ስምምነቱ ትልቅ ትርጉም አለው። ሕይወቱን፣ ንብረቱን በማጣት፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ በከፋ መልኩ ለተጎዳው ትግራይ ሕዝብ የበለጠ እርካታ የሚሰጥ ነው።

ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሥነልቦናዊ ጫና ስር ወጥቶ ለማገገም ብዙ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ስምምነቱ በፍጥነት ወደ ተግባር መቀየር አለበት ብለዋል። የትግራይ ሕዝብ በሠላም ስምምነቱ ብቻ በተስፋ ማደር መጀመሩን ጠቁመው፣ በስምምነቱ ውጤት ለዘላቂ ሠላሙ እንደሚመለስ ገልጸዋል።

አንዳንድ የውጭ ኃይሎች የአፍሪካ ኅብረት የሰላም ስምምነቱን እንዳይመራ በተለያዩ ምክንያቶች ሲያደናቅፉ መቆየታቸውን አስታውሰው የአፍሪካ መሪዎች በቁርጠኝነት ጉዳዩን የራሳቸው በማድረግ ሠላም ስምምነቱን በመልካም እንዲቋጭ በማድረጋቸው ሊቀመንበሩ አመስግነዋል።

አፍሪካውያን የውጭ ጫና በመቋቋም ለማደራደር የከፈሉት መስዋዕትነት አፍሪካውያን ያለማንም ጣልቃገብነት ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት



እንደሚችሉና አፍሪካ ነፃነቷን አስጠብቃ የምትቀጥል ስለመሆኗ ትልቅ መልዕክት ያስተላለፈ የሰላም ስምምነት ነው ብለዋል ዶክተር አረጋዊ በርሄ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም የራሱን ችግር ያለማንም ጣልቃ ገብነት በራሱ መፍታት የጀመረው ዛሬ ሳይሆን የዓባይ ግድብ ግንባታ ጭምር ነው ያሉት ዶክተር አረጋዊ ፤ አሁንም ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የሰላም ስምምነቱ መጠናቀቁ ትልቅ አንደምታ አለው ብለዋል።

ኅብረተሰቡ ጽንፈኝነትና አክራሪነት መንፈስ የተጠናወታቸውና የግል ጥቅማቸውን ማዕከል በማድረግ ኅብረተሰቡን አደጋ ላይ የሚጥሉ አስተሳሰቦች የሚያራምዱ ቡድኖችና ግለሰቦችን በማጋለጥ ስምምነቱን ወደ መሬት ለማውረድ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የራሱን ችግር በራሱ የመፍታት ባህሉን አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች ይህንን ስምምነት ስኬታማ ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽዎ ማበርከት ስለሚጠበቅባቸው የበኩላቸውን አስተዋጽዎ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበው ጥቅማቸውን ማዕከል በማድረግ ችግሮችን ከሚያባብሱ ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች ኅብረተሰቡ ተደራጅቶ ሊታገላቸው ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

## የአርቲስት አሊ ቢራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሥርዓት አስመልክቶ ከፌዴራል መንግሥት፣ ከኦሮሚያ ክልል፣ ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተውጣጣው የአብይ ኮሚቴ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

የአርቲስት አሊ ቢራን የቀብር ሥነ ሥርዓት መርሀግብር አስመልክቶ መግለጫ የሰጡት የመንግሥት ኮሙኒዩኬሽን አገልግሎት ሚኒስቴር ዴኤታና የአብይ ኮሚቴው አባል አቶ ከበደ ዴሲሳ እንደገለጹት፤ የክብር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራን በሞት ማጣት ለመላ ኢትዮጵያውያን ከባድ ኀዘን ነው።

አቶ ከበደ እንደገለጹት፤ አርቲስት አሊ ቢራ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ በድንቅ ብቃት ሙያና ክህሎት ለአርት ኢንዱስትሪው የተለየ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል። በፍቅርና በወንድማማችነት ላይ የሠራው ሥራ ጀግና የሚያስብለው በመሆኑ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ በጀግና አሸኛኘት የሚከናወን ይሆናል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በሙዚቃ ሥራው ስለ ፍቅር፣ ወንድማማችነት፣ ስለ አብሮነት፣ ስለ ፍትህና ነፃነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ለፍትና ለነፃነት ታግሏል፣ አታግሏል።

በአርቲስቱ ሞት የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ኀዘን ተሰምቶታል። ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና ለአፍቃሪያቸው በሙሉ መጽናናትን እንመኛለን። አርቲስቱ በአገራችን ለስልሳ አመታት ለአርት ኢንዱስትሪው ጉልህ ሚና ነበራቸው። ይበልጥ በኦሮሚኛ ሙዚቃው ይታወቅ እንጂ በብዙ ቋንቋዎች አቀንቅኗል፤ ለአብነትም በአፋርኛ፣ በአደሬኛ፣ በአማርኛ፣ በሱማሌኛና በሱዳንኛ በመጫወት ለአርቱ እድገት ከፍተኛ ሚና ነበረው ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊና የኦሮሚያ ንዑስ ኮሚቴ አስተባባሪ አቶ ሞገስ ኢደኤ በበኩላቸው፤ አርቲስቱ በሕይወት በነበረበት ወቅት መንግሥት ከፍተኛ የሆነ እገዛና እንክብካቤ ሲያደርግለት ቆይቷል ብለዋል።

ዛሬ ከጠዋት ሁለት ሰዓት ጀምሮ ቢሾፍቱ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ወደ አዲስ አበባ እንደሚሸኝና በአዲስ አበባ ወዳጅነት አደባባይ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የሥራ ባልደረቦቹና አድናቂዎቹ በተገኙበት አርቲስቱን የሚመለከቱ ፕሮግራሞች እንደሚካሄድም አስባባሪዎቹ ገልጸዋል።

በመቀጠል ወደ ትውልድ ስፍራው ድሬዳዋ የጀግና የክብር ሽኝት እንደሚደረግለት ገልጸው፣ አስከሬኑ ወደ ድሬዳዋ ካቀና በኋላ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የሶላት ሥነ ሥርዓት በማድረግ ከስምንት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ይፈጸማል ሲሉ ገልጸዋል።

የአብይ ኮሚቴው አባል እና የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር ፕሬዚዳንት አርቲስት ዳዊት ይፍሩ በበኩሉ፤ ኢትዮጵያ የወላድ መካን አይደለችም። በርካታ ጀግኖች አሏት፣ ከዚህም ውስጥ አንዱ አርቲስት አሊ ቢራ ነው ብሏል።

ከዚህ በኋላ የአሊ ቢራን ሥራ በመተንተንና በማስተዋወቅ ትውልድ እንዲማርበት ማድረግ ያስፈልጋል ያለው አርቲስት ዳዊት፤ ላለፉት ስድስት አስርት አመታት አሊ ቢራ ሙዚቃው ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓል። ሙዚቃ ውስጥ መግባት ነውር በሆነበት ጊዜ ስለ ሙዚቃ በማስተማር የተሳሳተ አመለካከትን ቀይሯል ብሏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አፍሪካውያን የችግሮቻቸው መፍትሄ ባለቤት ናቸው!

በአፍሪካውያን ላይ ከቅኝ አገዛዝ ማግስት ጀምሮ ከተፈጠሩ እና ትርክቶች ዓለም አቀፍ መድረኮችን ካጣበቡ እውነታዎች አንዱ አፍሪካውያን ለችግሮቻችው መፍትሄ የመሆን አቅም እና ተነሳሽነት የላቸውም የሚለው ነበር።

በርግጥ አፍሪካውያን የቅኝ አገዛዝን ከፍ ባለ ተጋድሎ አሽቀንጥረው ከጣሉ ማግስት ጀምሮ ያጋጠሟቸው ችግሮችም ሆኑ፤ እንደመፍትሄ የሄዱባቸው መንገዶች አፍሪካዊ ስለመሆናቸው ተገቢውን እውቅና ያገኙ አይደሉም።

አፍሪካውያን ከነፃነት ትግሉ ዋዜማ ጀምሮ ነፃነታቸውን ሙሉ አድርጎ በስኬት ለማጠናቀቅ የሄዱበት እልህ አስጨራሽ ትግልና ትግሉ ያስከፈለው ዋጋ በአብዛኛው ቅኝ ገዥዎች የፈጠሩትን ችግር ለማረቅ እንደሆነ ይታወቃል።

ችግሩን ለመፍታት የነበረው ትልቁ ተግዳሮትም ችግሩን ለመፍታት አፍሪካውያን የዕድሉ ባለቤት አለመሆናቸውና ዕጣ ፈንታቸውን በሚወሰነው የችግሮቻቸው መፍትሄ ውስጥ ባይተዋር የመሆናቸው እውነታ ነው። ይህ ደግሞ በየትኛውም የአህጉሪቱ ክፍል ለተፈጠሩ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ የመፍጠር አቅም አጥቶ ቆይቷል።

ከዚህም በላይ አህጉሪቱ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ የሁከትና ያለመረጋጋት፤ የጦርነትና የስደት ትርክት ማሳመሪያ እንድትሆን አስገድዷታል። ሌሎች በሚያስቀምጡላት ከማህበረሰባዊ ስሪቷ ያፈነገጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ዋጋ ስትከፍል እንድትኖርም አድርጓታል።

በርግጥ አፍሪካውያን ለችግሮቻችው እራሳቸው መፍትሄ እንደሚሆኑ ከነፃነት ዋዜማ ጀምሮ «በፓን አፍሪካኒዝም» ንቅናቄያቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙና ሲጮሁ ነበር። ለዚህ የአህጉሪቱ ሕዝቦች ድምጽ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱም ጥቂቶች አይደሉም።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ለማቋቋም በወቅቱ የነበሩ አፍሪካውያን አባቶቻችን ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱትና ብዙ ጣልቃገብነትን ያስተናገዱትም ከዚህ እውነት በመነጨ ነው። እውነታውን በጽናት ታግለው ማሸነፍ የቻሉትም አፍሪካውያን ለችግሮቻቸው መፍትሄ የመሆን አቅም ባለቤት ስለሆኑ ነው።

ከዚህ ድምጽ በስተጀርባ ያለው በራስ የመተማመንና የውጭ ጣልቃ ገብነትን የመቃወም አዝማሚያ ብዙ ያላስደሰታቸው ኃይሎች በወቅቱ ድምጹን ለማፈን የሄዱበት መንገድ አፍሪካውያንን ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ እውነታውን ሊቀይረው የቻለ አይደለም።

ዛሬም ቢሆን የአፍሪካውያን ለራሳችን ጉዳይ ራሳችን አናንስም የሚለው ሀሳብና ከሀሳቡ በስተጀርባ ያለው በራስ የመተማመን መንፈስ ዕረፍት የሚነሳቸው ኃይሎች የአፍሪካውያን ጉዳይ ዋነኛ ባለቤት ለመሆን የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት በአዲስ መልኩ እና በተጠናከረ መንገድ እንደቀጠለ ነው።

መንግሥታትን፣ ዓለም አቀፍ ተቋማትን እና የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም በአፍሪካውያን ጉዳይ ከአፍሪካውያን በላይ ሆነው ለመታየት ሲሞክሩ እየተስተዋለ ነው፣ አፍሪካውያን ተረጋግተው እና በሰከነ መንፈስ፤ ባህላቸውን፣ እምነታቸውን እና ማህበራዊ እሴቶቻችውን ታሳቢ አድርገው ለችግሮቻቸው መፍትሄ እንዳይሆኑ ተግዳሮት እየሆኑ ነው።

ይህ እውነታ ዓለም አቀፍ መድረኮችን አጣቦ በያዘበት አሁነኛ እውነታ፤ አፍሪካውያን ለችግሮቻቸው እራሳቸው መፍትሄ የመሆናቸው ነገር ዛሬም የአፍሪካውያን ድምጽ ሆኖ መሰማት ከጀመረ ውሎ አድሯል። አፍሪካውያን ከቀደመው ትውልድ በተሻለ መረዳትና መነቃቃት ለችግሮቻችው መፍትሄ መሆን እንደሚችሉ በተጨባጭ ማሳያነት የቻሉበት የታሪክ ምዕራፍ ውስጥም ገብተዋል።

ለዚህ ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የነበረ፤ አገርና ሕዝብን ብዙ ዋጋ ያስከፈለ ግጭት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የወሰዱት ኃላፊነትና የተደረሰበት የሰላም ስምምነት ትልቅ ማሳያ ነው።

የተደረሰበት የሰላም ስምምነት የአንድ ወገንን አሸናፊነት /ተሸናፊነት ያጸና ሳይሆን፤ አገርን (ኢትዮጵያን) እንደ አገር አሸናፊ ያደረገ መሆኑ ደግሞ፤ ስምምነቱ የቱን ያህል ዘላቂ ሰላም የማምጣት አቅም እንዳለው ያመላከተ ነው።

ይህ ተጨባጭ ተሞክሮ የዛሬው አፍሪካዊ ትውልድ የቀደሙት አባቶቹ መንፈስ እንደተጋባበት ፤ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት ባለቤት እየሆነ እንደመጣ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ለራሱ ችግር የመፍትሄ ባለቤት መሆኑንም በተግባር ያሳየ ነው።

የሰላም ስምምነቱ አፍሪካውያን ትናንት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለራሳቸው ችግሮች የመፍትሄ ባለቤት ስለመሆናቸው ሲያሰሙት የነበረው ጩኸታቸው ሰሚ እንዲያገኝ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር፤ ከዚህም በላይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን በቃ ለማለት የሚያስችል ውጤታማ ተሞክሮ ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የሰላም ስምምነቱ

## - ወደ ቀደመው የተስፋ ዝማሪያችን ለመመለስ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በብርሃን የፈካ የኢትዮጵያ ጊዜ ላይ ነን። ብዙ ነገሮችን አሸንፈን፣ ብዙ ችግሮችን አልፈን ሊነጋ በከጃጀለው ሰማይ ስር ነን። ትላንትና ከነጉድፉ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ አለ። ያለፉት ጊዜያቶች ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አዳፋ ነበሩ። ሁሉን አልፈን፣ ሁሉን ተሻግረን እነሆ የኢትዮጵያ ጊዜ ላይ ደርሰናል። ዛሬ እንደትላንት አይደለም፣ አይሆንምም። ለውጥ በናፈቁ፣ ሰላም በተራቡ ነፍሶች አዲስ ማለዳን አይተናል።

ኢትዮጵያዊነት በሚያስጨንቃቸው አሸናፊ ልቦች አሸንፈናል። የኢትዮጵያ የመነሳት ጊዜ ላይ ነን። ትላንትን በነበር የምናስታውስበት፣ ችግሮቻችንን ጥለን ወደ ላቀ ሀገራዊ ማንነት የምንሸጋገርበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ እንገኛለን። በሰላም ድምጽ የትላንት የታላቅነት ገድላችንን መልሰን ዳግም ታሪክ የምንሠራበት ጫፍ ላይ ነን። እንደተመኘነው ሆኗል..ኢትዮጵያ በልጆቿ አሸንፋለች። ኢትዮጵያ በሰላም አሸንፋለች፡፡

ከዚህ በኋላ ያለው የከፍታ ዘመን ነው። ስለ ኢትዮጵያ የሚያወጉ ድምፆች በዓለም ዙሪያ እየተሰሙ ነው። የአፍሪካ ኅብረትን ጨምሮ የተባበሩት መንግሥታትና የአውሮፓ ኅብረት ስለ ኢትዮጵያ ሰላማዊ ምክክር ደስታቸውን ገልጸዋል። አሁን ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት እየሄደባቸው ያለውን ሀገራዊ ስትራቴጂ የሚያደንቁና የሚያበረታቱ ሀገራት በዝተዋል።

የኢትዮጵያን ጥቅምና ሉዓላዊነት በማይነካ መልኩ የተራመድንባቸው የሰላምና የድርድር ሂደቶች ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ አድርገዋል። የኢትዮጵያ ማሸነፍ የመላው ሕዝብ ማሸነፍ ነው። ስለሀገራችን ክብርና ሉዓላዊነት በአንድ ባንቆም ኖሮ በነዛ ሁሉ ጣልቃ ገብ ሀገራት ተከበን ቀና አንልም ነበር።

የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካውያን እንዲፈታ ያደረግነው ጥረት ፍሬ አፍርቶ እነሆ ሀገራችን ወደምትናፍቀው ሰላሟ ተመልሳለች። መንግሥት ከሕዝብ ጋር አብሮ በሁሉም መስኮች እየወሰዳቸው ያለው አመርቂ ውጤቶች ስለሀገራችን ምን ያክል እንደምንቆረቆር የሚያሳይ ሆኖ አልፏል፡፡

ይሄ የማሸነፍ ስነልቦና ሀገራችን ለያዘችው የለውጥና የብልጽግና ጉዞዋ ወሳኝ ነው፤ በበረታ መንፈስ ልንቀጥለው ይገባል። ወደፊት ተባብረን የምናሸንፋቸው የድህነትና የኋላቀርነት ነውሮች አሉብን። ከሰላም ውጪ በምንም የማይረቱ በርካታ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች አሉብን። መፍትሔአቸው ሰላምና መነጋገር፣ አንድነትና ወንድማማችነት የሆኑ ብዙ ሀገራዊ አጀንዳዎች አሉን።

**ኢትዮጵያዊነት በሚያስጨንቃቸው አሸናፊ ልቦች አሸንፈናል። የኢትዮጵያ የመነሳት ጊዜ ላይ ነን፡፡ ትላንትን በነበር የምናስታውስበት፣ ችግሮቻችንን ጥለን ወደ ላቀ ሀገራዊ ማንነት የምንሸጋገርበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ እንገኛለን**

ከሰላምና ከእርቅ ውጪ ሊታደጋቸው የማይችል እልፍ ነቀርሳዎች በዙሪያችን አሉ። እናም በአንድነት ያመጣነው የአሁኑ የሰላም ጸሐይ ለነገይቱም ኢትዮጵያ እንዲበቃ በችግሮቻችን ላይ መነጋገርን እናስቀድም። እርቅና ሀገራዊ ተግባቦትን እናስቀድም። ያለፍናቸው ሁለት ዓመታት ሰላም አጥተን በብዙ ነገር ላይ የባከነባቸው ናቸው። ካለፈው ተምረን መጪውን ጊዜ መልካም ለማድረግ በሰላም ማሸነፍን፣ በአንድነት ማሸነፍን መለማመድ አለብን፡፡

ኢትዮጵያን ነጻ ላወጡ..ባሉበት ቦታ ሁሉ ስለሀገራቸው ለጮሁ ለነዛ ነፍሶች ክብር ይግባቸው። ለጠላቶቿ ንክሻ ላልተዋት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ምስጋና ይገባል። ባዕድ ሆነው ወዳጅ ለሆኑንም እንደ ቻይናና ሩሲያ ላሉ ሀገራትም ክብር አለን። መቼም የማንረሳቸው የኢትዮጵያ የመከራ ወዳጆች ናቸው። ኢትዮጵያ በምታደርጋቸው ማናቸውም ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ከፊት በመሆን ሲተባበሩን ያሉ ሀገራት ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ውለታ አትረሳም።

ለነዚህ ሀገራት ያላትን ክብርና ምስጋና በተለያየ ጊዜ ገልጻለች.. አሁንም ልታመሰግናቸው ትፈልጋለች። በህዳሴ ግድባችንም ሆነ መንግሥት በትግራይ ክልል እየወሰደ በነበረው የሕግ ማስከበር ሥራ ላይ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሚደርሱብንን ጫናና ጣልቃ ገብነት ሲኮንኑና ሲከላከሉልን ነበር። ያኔ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሙሉ በሙሉ ማክበር እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተው ሲከራከሩልን ነበር፡፡

ትንሳኤያችን ከዚህ በኋላ ነው። የኢትዮጵያ ጊዜ ላይ ነን። የኢትዮጵያ ጊዜ ላይ እንደመሆናችን ብዙ የምንሰማቸው የክብርና የከፍታ ድምፆች ይኖራሉ። የሰላምን ጣዕም አውቀንዋል። ሰላም ርቆን በሰነበትንባቸው ዓመታት ውስጥ የሰላምን ዋጋ ተረድተናል ። አሁንም ከሰላም ውጪ ምንም ክብርና ከፍታ እንደሌለን በማመን በአንድ ሀገር ላይ አንድ ሆነን መኖር የመጨረሻ ምርጫችን ይሆናል።

እስከዛሬም የራሳችን ጠላቶች ራሳችን ነበርን። አሻጋሪ በሌለበት የሰላም ድልድያችንን ሰብረን ለመሻገር ስንዳክር ኖረናል። ጥቅም በሌለበት ስንሞትና ስንገዳደል ኖረናል። ጨለማ ውስጥ ሆነው ብርሃን ስንጠብቅ ብዙ ጊዜ አልፎናል። አሁን ይበቃናል..እኛም ሆንን ሀገራችን ብርሃን የምታይበት ጊዜ ነው። ባጣነው ሰላም ልክ፣ ባጣነው ወንድማማችነት ልክ ሁሉንም የምናገኝበት ጊዜ ነው። መጪው ጊዜ በብርሀን ውስጥ የምንመላለስበት የክብር ጊዜ ይሁንልን፡፡

ወደ 6ኛው ገጽ ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

## የሰላም ስምምነቱ…

ከገጽ 5 የዞረ

ለሀገራችን ሙሴን እንሁን። ለመከራዋ ተጨማሪ መከራ ሳይሆን ችግሯን የምትሻገርበትን መላ እንፍጠር። ሙሴ አንድ ሆኖ ብዙዎችን ከባርነትና ከግዞት ያወጣ ሰው ነው። ሰላም ወዳድ የፍቅር ሰው ከሆንን ሙሴን መሆን አይቸግረንም። ሙሴነት በሰላም የሚመጣ ነው። ሙሴነት ፍቅርን ከማወቅ የሚጀምር ነው። ሙሴነት በአንድነትና በመተባበር የሚገኝ ነው፡፡

እያንዳንዳችን ሰላም ወዳድ በሆነ ልብና ፍቅርን በሚያመልክ ማንነት ሙሴን መሆን እንችላለን። ለከእንግዲኋ ኢትዮጵያ እንደ ሙሴ ያለ ሀገር ወዳድና ሰላም ናፋቂ ነፍስ ነው የሚያሻት። ለብዙ ጊዜ ሰላም አጥታ ፍቅር ርቋት ኖራለች አሁን ግን ሙሴን የምንሆንበትና ሀገራችንን ከኋላቀርነት የምናላቅቅበት ጊዜ ነው። ትላንት በብዙ ምስቅልቅል ውስጥ ነበርን። ሙሴን የመሰለ..እንደ ሙሴ የሆነ ባህር አሻጋሪ አጥተን ተስፋ እየናፈቅን፣ ከባህሩ ወዲህ ማዶ ቆመን ከባህሩ ወዲያ ማዶ ያለውን ከንዓንን ስንናፍቅ ነበር። ዛሬ ወደናፈቅነው ከነዓን መጥተናል። ዛሬ ወደናፈቅንው ሰላምና እርቅ ተሸጋግረናል። መጪው ጊዜ እንደዚህ ሆኖ እንዲቀጥል ሙሴነታችንን እንዳናጣ መትጋት አለብን፡

የኢትዮጵያ ጊዜ ላይ ነን። በፈካና ተስፋ በተሞላ እውነት ውስጥ። የምንናፍቀውን አግኝተናል። ግን ገና ነን..ብዙ የምንናፍቃቸው ነገሮች አሉ። ደስ የሚለውና የሚያኮራው ደግሞ እነዛ የምንናፍቃቸው ብዙ ነገሮች በሰላም ውስጥ መገኘታቸው ነው። ዋናውን ከያዝን አያሳስብም..ዋናው ነገር ሰላም ነው። ሰላም ባለበት ቦታ ሁሉም ነገር አለ። የምንናፍቃቸው ነገሮች የእኛ እንዲሆኑ ሰላማችን መቀጠል አለበት።

መጪውን ጊዜ በሰላምና በሀገራዊ ተግባቦት ውስጥ ማለፍ ግድ ይለናል። ብዙ ተስፋ የሰነቅን ሕዝቦች ነን። እንዲሆንልን የምንፈልገው ብዙ ነገር አለ። እንደ ሀገር እንደ ዜጋ የሚያምረን ብዙ ነገር ነው። እኚህ ሁሉ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተስፋዎቻችን እውን እንዲሆኑ ይቅር ባይ ልብ ያስፈልገናል። ችግሮቻችንን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን ባህል ማድረግ ይጠበቅብናል። የሀሳብ ልዩነት፣ የፖለቲካ ልዩነት ሲፈጠር ጦር መማዘዝ ሳይሆን በአንድ ሀገር ላይ ስለ አንድ ሀገር እያሰብን እንደሆነ በመረዳት ልዩነቶቻችንን በምክክር ማጥበብን እንልመድ። በትናንት ስህተቶቻችንም እንማር ።

ባጣንው ልክ የምናገኝበት፣ በወደቅንው ልክ ቀና የምንልበት፣ በከሰርነው ልክ የምናተርፍበት ቀናት ከፊታችን አሉ ። ትላንት ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል ..በብዙ ነገር ልባችንን ተሰብሯል። አንድና አንድ የሚያስፈልገን ሰላም እንደሆነ ከሁሉም በላይ አስተምሮናል። አሁን ከትናንት ተምረን ስለ ሰላም ተጠንቅቀን የምንኖርበት ጊዜ ነው። አሁን በተረዳንው ሐቅ ውስጥ የምንቆምበት ጊዜ ነው፡፡

ሰላም ያጣንባቸውን እነዛን የመከራ ጊዜያቶች እያሰብን ሰላማችንን ላለማጣት ተጠንቅቀን የምንኖርበት ጊዜ ላይ ነን። ሰላም አንድ ጊዜ ከእጅ ከወጣ ዋጋ ሳያስከፍል አይመለስም። ያለፉት ሁለት ዓመታት ሰላማችን ከእጃችን ወጥቶ ምን ያክል ዋጋ እንዳስከፈለን እኛው ምስክር ነን። እንደ ሀገር ብዙ የልዩነት ሀሳቦች ሊኖሩብን ይችላሉ።

እንደ ሀገር ብዙ ፈተናዎችን እያስተናገድን ሊሆን ይችላል ሰላም ካለንና ለሰላም ቅድሚያ ከሰጠን ችግሮቻችን አይበልጡንም። አሁን ላይ ችግር የሆነብን በችግሮቻችን መበለጣችን ነው። ሁሉም ችግሮቻችን ሰላም የሚያሳጡን፣ የሚያገፉፉን መሆናቸው ነው። ካለፈው ተምረን ችግሮቻችንን ለሰላም ማጣት ሳይሆን ሰላማችንን ለችግሮቻችን እንጠቀም፡፡

ለሀገር ሰላም መንግሥት እንደ መንግሥት የሚሠራው አለ። እያንዳንዱ ዜጋም እንደ ዜጋ የሚያደርገው  የማይተካ አስተዋጽዖ አለ። ሁላችንም ባለን እውቀትና በተሰጠን መክሊት በመጠቀም ለሀገራችን ምርጡን በማድረግ የመንጋቷን ዘመኗን ማፍጠን እንችላለን።

ሰላም የአንድ ወገን ብቻ የቤት ሥራ አይደለም። ሰላም ከመንግሥት ብቻ የሚጠበቅም አይደለም ። ከዚህ ይልቅ ከአጠቃላይ ሕዝባችን ማኅበረሰባዊ ስብዕና የሚጠበቅና በዚሁ ላይ የሚመሠረት ነው ። እንደ ሀገር የሰላማችን ፈጣሪዎችና ጠባቂዎች እኛ ነን። ምሽት ላይ ቆመው በሌሎች የተፈጠረን ንጋት መጠበቅ አደራ በልነት ነው። እውቀታቸውን ሸሽገው በሌሎች ጥበብ የተፈጠረን ብርሃን ማንጸባረቅ ነውር ነው። ለሀገራችን መንጋት ሁላችንም አስተዋጽዖ ማድረግ ከቻልን የጋራችንን የማይመሽ ቀን መፍጠር እንችላለን፡፡

ያለነው በለውጥ ወቅት ነው ፤የፈተናዎች ብዛት የወቅቱን ባህሪ አይለውጡትም ። ለዚህ ቀድሞ ችግሮችን በንግግር ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችና የሚገኙ ተስፋ ሰጭ ውጤቶች ለውጡን የማስቀጠል ወሳኝ አቅም ናቸው። ሀገር በጥቂት ሰዎች ኃይልና ብርታት አትለወጥም። ለውጥ የብዙኃኑን ፍቃድ ይፈልጋል። በአንድ ወገን ፍቃድ ብቻ ንጋት የለም።

በጀመርንው የሰላም መንገድ ከተጓዝን ንጋታችን ሩቅ አይሆንም። ገና ከፍ እንላለን። ገና ከዚህም በላይ ዓለም ያውቀናል። ገና በጠላቶቻችን ላይ ከፍ ብለን የምንታይበት ጊዜ ይመጣል። ከፊታችን ሰላምን የለበሱ በርካታ የመንጋት ዘመኖች አሉ። የህዳሴ ግድባችን ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ሊያወጡን የሚችሉ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ነው።

በዛ ላይ እርቅ ወርዷል..ወደ ሰላማችን ተመልሰናል። እነዚህ ሁሉ የከፍታችን ማሳያዎች ናቸው። ያለምንም ጥርጥር በኢትዮጵያ ጊዜ ላይ ነን። ዳግም ጥፋት እንዳይመጣ መትጋት ይኖርብናል። ለሀገራችንም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ አዲስ ነገር ለመሥራት አሁን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ምቹ ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

እጆቻችንን ለሥራ፣ አዕምሯችንን ለበጎ ሀሳብ በማሰልጠን ብሩህ ነጋችንን መገንባት እንጂ ጊዜ ባለፈበት ለየትኛውም ወገን በማይጠቅም ጦርነትና ንትርክ ጊዜን ማባከን ለዚህ ዘመን የማይመጥን ተግባር ነው፡፡

እውቀታችንን እና መክሊታችንን በመጠቀም የተጀመረውን የሰላም ጥረት ውጤታማ ለማድረግ የያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ከፍ ያለ ነው ፤ይህን ኃላፊነት መወጣት የተጀመረውን ለውጥ በማስቀጠል ሀገራዊ ብልጽግናን እውን ለማድረግ አቅም የመሆን ያህል ነው ።ለመጪው ትውልድ የጠሸለች ሀገር ለማስረከብ የሚያስችል የመሠረት ድንጋይ የማኖር ጭምር ነው ።

እኔ የሚጠበቅብኝን ሁሉ እንደ አንድ ዜጋ ለማበርከት በዝግጅት ላይ ነኝ። እናተም የሚጠበቅባችሁን በማድረግ ለራሳችሁም ሆነ በእናንተ በኩል ለሚመጣው ትውልዳችሁ መልካም ቤትን መሥራት ይጠበቅባችኋል ። ይሄ ሲሆን ብቻ ነው ሰላም የሚመጣውና የመጣውን ሰላም ማስቀጠል የምንችለው፡፡

ጥሩዋና መልካሟ ኢትዮጵያ ያለችው በጥሩውና በመልካሙ እኔና እናንተ ውስጥ ነው። ዘመናዊቷና ስልጡኗ ኢትዮጵያ ያለችው ሰላም ወዳድ በሆነ ሕዝቦቿ ጉያ ውስጥ ነው። ከትላንት እስከ ዛሬ ለሀገራችን እንዲህ መሆን ተጠያቂው እኛው ነን። ልቡን ከፍቅር፣ እጆቹን ከልማት፣ አዕምሮውን ከሰላም አሸሽቶ ታላቅ ሀገር የመሰረተ ሕዝብ የለም ።

> **ኢትዮጵያን ነጻ ሳወጡ.. ባሉበት ቦታ ሁሉ ስለሀገራቸው ስጮሁ ስነዛ ነፍሶች ክብር ይግባቸው። ስጠላቶቿ ንክሻ ሳልተዋወት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ምስጋና ይገባል ። ባዕድ ሆነው ወዳጅ ስሆኑንም እንደ ቻይናና ሩሲያ ሳሉ ሀገራትም ክብር አስን**

ሁላችንም እንደ ዜጋ የሚጠበቅብንን መወጣት በሚያስችል ሁለንተናዊ ቁመና ላይ ከተገኘን አይደለም ለራሳችን ለሌላውም የሚተርፍ አቅምና ሞራል ያለን ሕዝቦች ነን። ወደጀመርነው ፤ወደ ቀደመው የተስፋ ዝማሪያችን የምንመለሰውና መጭውን ትውልድ የተሻለ ሀገር ተረካቢ ልናደርገው የምንችለው በይቅርታ መንፈስ ለተደረሰበት የሰላም ስምምነት አቅም መሆን ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ መንፈሳዊና ማኅበራዊ እሴቶቻችን ትላልቅ ጉልበቶቻችን ናቸው ። ሰላም እንሁን፣ ሰላም እናድርግ፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# ጠንካራ የበይነ መረብ አስተዳደር - ለቴክኖሎጂ ዘርፍ ደህንነት

**አንተነህ ቸሬ**

የታሪክና የጊዜ ሂደት የሰውን ልጅ ከኢንተርኔት (በይነ-መረብ) ውጭ ሆኖ መኖር እጅግ አስቸጋሪ፣ ምናልባትም የማይቻል፣ የሆነበት ዘመን ላይ አድርሶታል። ዓለምን ያለኢንተርኔት ለማሰብ፣ ትውስታንና ግንዛቤን ወደ መጀመሪያዎቹ የሰው ልጅ የዝግመተ-ለውጥ ደረጃዎች በመመለስና በማሰላሰል ማሰብ ሳይሻል አይቀርም።

‹‹የቴክኖሎጂ ዘመን›› የሚባለው የአሁኑ ጊዜ፤ የረቀቀውን ሰው ሠራሽ የልኅቀት ቴክኖሎጂ (Artificial Intelligence) በመጠቀም የሰውን ኑሮ ቀላል ያደረጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙበት ወቅት ነው ሀገራትም መጭውን ጊዜ በማሰብ ቴክኖሎጂን እንደዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በመያዝ ምጣኔ ሀብታቸውን በቴክኖሎጂ የሚታገዝ እንዲሆን ጥረት እያደረጉ ነው።

በአሁኑ ወቅት ቀልጣፋና ውጤታማ የሥራ እንቅስቃሴን ከኢንተርኔት ነጥሎ ማሰብ አይቻልም ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ተግባቦቶችና ግብይቶች መሰረታቸውን በኢንተርኔት ላይ አድርገዋል ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከፈጣንና አስተማማኝ የኢንተርኔት አገልግሎት ብቻም ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ከኢንተርኔት አገልግሎት ውጭ የሆነው የዓለም ሕዝብ ቁጥር የኢንተርኔት ተጠቃሚ መሆን ከቻለው ጋር የሚስተካከል እንደሆነ የዓለም አቀፍ የኢንተርኔት ጉባኤ መረጃዎች ያሳያሉ።

ቴክኖሎጂ እያንዳንዱን የዓለምን እንቅስቃሴ በተቆጣጠረበት በአሁኑ ወቅት፣ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ከቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት ውጭ ማሰብ የሚቻል አይሆንም ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለማችን ቁንጮ የሆኑት ልዕለ ኃያላን ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፋቸው እጅግ የተራቀቀ ነው የቴክኖሎጂ ፈጠራና ስርጭት ደግሞ ያለኢንተርኔት መሰረተ ልማት አቅርቦት አይታሰብም በተለይ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴያቸውን ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ ባሸጋገሩ ሀገራት የዜጎች ዕለታዊ እንቅስቃሴ ያለኢንተርኔት የሚታሰብ አይሆንም በእነዚህ ሀገራት የዜጎች ተግባቦት፣ ግብይትም ሆነ የስራ ግንኙነት ኢንተርኔትን መሰረት ያደረገ ነው።

ዘመኑ በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በየጊዜው ይፋ የሚሆኑበት የታሪክ ምዕራፍ በመሆኑ፣ ከቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ዓይነተ ብዙና ውስብስብ ችግሮችም ይስተዋላሉ በየጊዜው ይፋ የሚደረጉት የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሰዎችን ሕይወት ቀላል ለማድረግ ሚናቸው የላቀ ቢሆንም፣ ከቴክኖሎጂዎቹ ጋር የሚፈጠሩት ችግሮች ደግሞ ቀላል የማይባሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ያሳርፋሉ ስለሆነም የቴክኖሎጂ ትሩፋቶች የሚያስገኟቸውን እድሎች በሚገባ ለመጠቀም እና ቴክኖሎጂ ወለድ ችግሮች የሚፈጥሯቸውን ጫናዎች ለመቀነስና ለማስወገድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መፍጠር ይገባል ይህን ለማሳካት ደግሞ የኢንተርኔት አስተዳደርን (Internet Governance) በሚገባ መምራት ያስፈልጋል።

የኢንተርኔት አስተዳደር ከኢንተርኔት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የመምራት ተግባር ሲሆን፣ በቴክኖሎጂ ውጤቶች እና ኢንተርኔት ተኮር በሆነው የሰዎች አለታዊ እንቅስቃሴ መብዛት ምክንያት ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረትና ክትትል የሚያስፈልገው ጉዳይ ሆኗል።

የኢንተርኔት አስተዳደር በአሁኑ ወቅት የዓለም ሀገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውንና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ትልቅ ትኩረት እየሰጧቸው ካሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ከሆነው ከሳይበር ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው የሳይበር ዘርፍ ሀገራት የቴክኖሎጂ የበላይነታቸውን ለማሳየት ጭምር የሚጠቀሙበት መሳሪያ ከሆነ ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ተቆጥረዋል በፖለቲካና ምጣኔ ሀብት ጉዳዮች አለመግባባት ውስጥ የገቡ ሀገራት አንዱ የፍልሚያ ግንባራቸው የሳይበሩ ዘርፍ ሲሆን መመልከት እየተለመደ ነው ሀገራት በሳይበር ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልቆ በመገኘት በሌሎች ሀገራት ላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ስነ ልቦናዊ ጫና ለመፍጠር እልህ አስጨራሽ ፉክክር በማድረግ ላይ ናቸዉ።

> **ቴክኖሎጂ እያንዳንዱን የዓለምን እንቅስቃሴ በተቆጣጠረበት በአሁኑ ወቅት፣ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ከቴክኖሎጂው ዘርፍ እድገት ውጭ ማሰብ የሚቻል አይሆንም ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለማችን ቁንጮ የሆኑት ልዕለ ኃያላን ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፋቸው እጅግ የተራቀቀ ነው**

የሳይበር ምኅዳር ዓለም አቀፍ ሉላዊነት እንዲፈጠር ያደረገ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ከሳይበር ምኅዳር ውጭ መሆን የማይታሰብ ሆኗል ያለ ሳይበር አቅም እንደሀገርም ሆነ እንደተቋም ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ ይቅርና ህልውናን ማስጠበቅ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል በአጠቃላይ ውጤታማ የሳይበር ቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ያላረጋገጠና የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት ያላስጠበቀ ሀገር ሉዓላዊነቱንና ብሔራዊ ጥቅሙን ማስጠበቅ የማይችልበት ወቅት ላይ ተደርሷል።

የኢንተርኔት አስተዳደርን ለመምራትና ለማቀናጀት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ በየዓመቱ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባዔ (Global Internet Governance Forum/IGF) ነው ጉባኤው እ.አ.አ በ2006 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ የተለያዩ ተሳታፊዎችንና ባለድርሻ አካላትን ወደ አንድ መድረክ በማምጣት ከበይነ-መረብ አስተዳደር ጋር በተያያዙ ፖሊስዎች ላይ ውይይት የሚካሄድበት መድረክ ነው መድረኩ ውሳኔ አመንጪና ሰጪ ለሆኑት ለግሉ ዘርፍና ለመንግስት የመረጃና የፖሊስ ሀሳብ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል ጉባኤው ከተለያዩ ሀገራትና ዘርፎች የተውጣጡ ተወካዮች ስለበይነ መረብ ዘርፍ እድሎችና ፈተናዎች የሚወያዩበት፣ መረጃ የሚለዋወጡበትና ልምድ የሚቀስሙበት እንዲሁም የጋራ ግንዛቤ የሚፈጠርበት መድረክም ነው።

ጉባኤው የኢንተርኔት መሰረተ ልማት ደህንነትንና አስተማማኝነትን የሚያመቻቹ የፖሊስ ጉዳዮችን ያነሳል፤ በታዳጊ ሀገራት ያለው የበይነ መረብ መሰረተ ልማት እንዲሻሻል፣ ባለድርሻ አካላት በበይነ መረብ አስተዳደር ላይ ያላቸው ሚና የተቀናጀ እንዲሆንና ለበይነ መረብ አስተዳደር የአቅም ግንባታ ግብአቶችንና ምክረ ሃሳቦችንም ያቀርባል።

በይነ-መረብ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ሁሉ ከመረጃ መረብ ወንጀሎች፣ ከጥላቻ ንግግሮች፣ ከሀሰተኛ ዜናዎች ስርጭት አኳያ የተለያዩ ጉዳቶችም አሉት ጉባኤውም እነዚህን ጉዳዮች በሕግና በሌሎች ማዕቀፎች መፍትሄ እንዲያገኙ ምክረ ሃሳቦች ይመላከቱበታል።

17ኛው ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት (በይነ መረብ) አስተዳደር ጉባኤ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ከሕዳር 19 እስከ 23 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ይካሄዳል ኢትዮጵያ 17ኛውን ይህን ጉባኤ እንድታዘጋጅ የተመረጠችው በቴክኖሎጂ ዘርፍ ለውጦችንና እድገቶችን እያስመዘገበች በመሆኑ፣ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ፀድቆ ወደ ስራ በመግባቱ፣ የተለያዩ የማሻሻያዎች የተደረጉበት የቴሌኮም ዘርፍ ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪዎች ክፍት በመደረጉ እና የቴሌኮምና የበይነ-መረብ ተደራሽነትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ በመሆኑ እንደሆነ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ።

ከዚህ በተጨማሪም በሀገሪቱ 56 ሚሊየን ገደማ የሞባይል እና ከ20 ሚሊዮን በላይ የበይነመረብ አገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎች መኖራቸውም ለጉባኤው አዘጋጅነት እንዳገዛትም ተገልጿል ጉባኤው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ሁነቶችን በብቃት የማዘጋጀት ልምዷን ለዓለም ከምታሳይባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱ እንደሚሆንም ተጠቁሟል።

በ17ኛው ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት ጉባኤ ላይ ከመላው ዓለም የተውጣጡ ከ2000 እስከ 2500 የሚደርሱ ተሳታፊዎች ይታደማሉ ተብሎ ይጠበቃል ጉባኤው ከሚመክርባቸው ጉዳዮች መካከል ከበይነ-መረብ ግንኙነት ውጪ የሆኑ ህዝቦችን ማገናኘትና ሰብዓዊ መብትን መጠበቅና ሰዎችን ከጥቃት መከላከል፤ ዳታን በአግባቡ ማስተዳደርና የግል ዳታ ጥበቃ፤ የተቆራረጠ የኢንተርኔት አገልግሎትን መቅረፍ፤ የኢንተርኔት ደህንነትን ማረጋገጥ፣ ጥበቃ ማድረግና ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲሁም የመጪው ጊዜ ቴክኖሎጂዎች የሆኑትና እንደ ሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) ያሉ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ።

የዘንድሮውን ጉባኤ የማስተናገድ ኃላፊነትን 16ኛውን ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ ካስተናገደችው ከፖላንድ የተረከበችው ኢትዮጵያ፣ ጉባኤውን በብቃት ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነች እንደምትገኝ ተገልጿል ከእነዚህ ተግባራት መካከል አንዱ ለዚሁ ዓለም አቀፍ ጉባዔ መሰረት ይጥላል የተባለውና ባለፈው ሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም የተካሄደው የመጀመሪያው ብሔራዊ የበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ ነው::

‹‹ኢንተርኔት ለአካታች ልማት›› በሚል መሪ ሀሳብ የተካሄደው ጉባኤው ስለበይነመረብ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞች እንዲሁም ተመጣጣኝ እና ትርጉም ስላለው የበይነመረብ ተደራሽነት መክሯል 17ኛውን ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ ስኬታማ ለማድረግ፤ በጉባኤው ላይ የሚካሄዱ ውይይቶች ሁሉን አቀፍ፣ ከዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተናበቡና ሃሳቦች በነጻነት የሚንሸራሸሩበት መድረክ እንዲሆን የኢትዮጵያ መንግስት ቁርጠኛ መሆኑ የተገለፀውም በዚሁ ብሔራዊ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባዔ ላይ እንደነበር ይታወሳል

ኢትዮጵያ 17ኛው ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ የአፍሪካ ሀገራት ከኢንተርኔት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ያሉባቸው ችግሮች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚጠቁም እና ለፖሊስ አውጪዎች መነሻ ሀሳብ የሚገኝበት እንዲሆን እንደሚሰራ በመጠቆም፣ የአፍሪካ ሀገራት በጉባኤው ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርባለች።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ሴክሬታሪያት የኢትዮጵያን የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ዝግጅት አድንቋል ሴክሬታሪያቱ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች እና ከኢትዮጵያ የበይነ መረብ አስተዳደር አዘጋጅ ኮሚቴዎች ጋር የመከረ ሲሆን፣ ሀገሪቱ ጉባኤውን ለማስተናገድ ላከናወነችው ተግባር አድናቆቱን ገልጿል።

ኢትዮጵያ ጉባኤውን በማስተናገዷ ታገኛቸዋለች ተብለው ከሚጠበቁት ጥቅሞች መካከል የሀገሪቱን መልካም ገጽታ፣ እድገትና አቅም ማስተዋወቅ፤ ሀገሪቱ የጀመረችውን የቴሌኮም ሪፎርም ኢንዲሁም በዘርፉ ያሉ ውጤቶችን ለሌሎች ሀገራት ማሳየት፤ ከተለያዩ ሃገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት እና የልማት አጋሮች ጋር ትስስር መፍጠር፤ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የሚሉት ይገኙበታል።

ከአዲሱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊስ ዓላማዎች መካከል አንዱ ምቹ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር እንዲፈጠር የሚያስችሉ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን መዘርጋት ነው ይህ ዓላማ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከበይነ መረብ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው ይህም የፖሊስው ውጤታማነት በበይነ መረብ አስተዳደር ብቃት እንደሚመዘን ማሳያ ይሆናል።

በሌላ በኩል ከአስር ዓመቱ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የልማት እቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት ነው ይህን ለማሳካት ደግሞ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ወሳኝ ግብዓት እንደሆነ ይታወቃል የዘርፉን ውጤታማነት ለማጎልበት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡት ግብዓቶችና አቅጣጫዎች መካከል የኢንተርኔት አቅርቦትና አስተዳደር ስራ አንዱ እንደሚሆን ይጠበቃል በዚህ ዘመን በተቋምም ሆነ በሀገር ደረጃ በኢንተርኔት አስተዳደርና ደህንነት ዘርፍ ተወዳዳሪ መሆን ካልተቻለ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናም ከባድ አደጋ ውስጥ እንደሚገባም አያጠራጥርም ስለሆነም አቅርቦቱም ሆነ አስተዳደሩ አስተማማኝና ውጤታማ የሆነ የኢንተርኔት መሰረተ ልማት እውን በማድረግ ሀገራዊ የልማት እቅዱን ለማሳካት ጥረት ማድረግ ይገባል ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ጦርነቱ ያስከተለውን የስነልቦናዊ ጉዳት ማከም

**ምሕረት ሞገስ**

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ኢጋጥሞ የነበረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥት ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ይህም ተሳክቶ በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በደቡብ አፍሪካ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተካሄደው የሰላም ንግግር ውጤት አምጥቶ የሰላም ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል።

ይሄ የሰላም ስምምነት ወደ መሬት እንዲወርድ፣ በሕዝቡ መካከልም ሰላማዊ ግንኙነቱና አንድነቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንዲሁም በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል በርካታ ሥራዎች በቀጣይ መሠራት እንዳለባቸው ይታመናል። ከሁሉም በፊት ግን የሕዝቡን ስነልቡና ማረጋጋት እና የይቅር ባይነትን መንፈስ ወደፊት ማምጣት ቀዳሚ ሥራ መሆን እንዳለበት የተለያዩ ምሑራን ይናገራሉ። የትኞቹ ሥራዎች ላይ ማተኮርና ቅድሚያ መስጠት ይገባል ስንል ያነጋገርናቸው ምሑራንም የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተውናል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ እና የሥነልቦና ምሑሩ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ፤ አካላዊ ጉዳት በወራት እና በዓመታት ይታከማሉ፤ ጠባሳ ትተው ያልፋሉ፤ አንዳንዶቹ ይሽራሉ፤ ቆይተው ይድናሉ የስነልቦና ጉዳት ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊሸጋገር ይችላል ይላሉ

« በአካል ከደረሰው ጉዳት እና ከወደመው ንብረት ይልቅ እኔን እጅግ የሚሳስበኝ የደረሰው የሕይወት መጥፋት ብቻ ሳይሆን አዕምሮ ላይ የደረሰው ስብራት ነው ሁልጊዜም እንደምለው በጣሊያኖች በየካቲት 12 አዲስ አበባ ላይ የተፈፀመው ጭፍጨፋ ይኸው በሶስተኛው ትውልድ ሳይቀር ይዘከራል አራተኛው እና አምስተኛው ትውልድም እየመጣ ነው መዘከሩ አይቀርም ይሔ ጦርነት ደግሞ እኛው በእኛው ነው ይሔ ሲታሰብ የአዕምሮ ስብራትን ማሰብ በራሱ ያሳምማል ለማከምም በጣም ብዙ ሥራን ይጠይቃል» ይላሉ የጦርነት ስነልቡና ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን ሲጠቅሱ፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን እንደሚያብራሩት፤ የአዕምሮ ስብራት በአንድ ትውልድ ላይ ብቻ የማይቆም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊሸጋገር የሚችል ትልቅ ጉዳይ ነው ስንል ጉዳቱ እጅግ ሰፊ፣ የተወሳሰበ እና ጥልቅ እንደሚሆን በማሰብ ነው

ሌላኛው የሥነ አዕምሮና የስነልቦና ባለሞያው ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር ሳሚ ወልዴ ፤ ጦርነት የሰዎችን አካላዊ ማንነት ብቻ ሳይሆን ሥነልቦና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ይናገራሉ ስነልቦና ስንል ስነመለኮታዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ እስከማስከተል ይደርሳል ሰዎች «የማመልከው ፈጣሪ እያለ እንዴት ይህ ይሆናል ? » በማለት ከሃይማኖት እና ከዕምነት ውጪ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ማኅበረሰቡን አጠቃላይ ሰዎችን የመጥላት አዝማሚያ ይኖራል ጨለማን መፍራት፣ ለመተኛት መስጋት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀላሉ መቆጣት፣ መናደድ፣ መበሳጨት፣ ለኅብረት እና ለጓደኝነት አለመመቸት የጦርነቱ ስነልቦናዊ ጉዳት ውጤት እንደሚኖር አያጠራጥርም ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከማኅበረሰብ መነጠል፣ ሁልጊዜም በተጠንቀቅ እና በስጋት ውስጥ መኖር፣ በተደጋጋሚ የጭንቀት ሆርሞን በመላው ሰውነት ስለሚሰራጭ በሕይወት ዘመናቸው ከሰዎች ጋር ከመብላት ከመጠጣት ይልቅ መጨነቅ እና መሸሽን የሚመርጡ ይኖራሉ ልባቸው ቶሎ ቶሎ የሚመታ እና የልብ ሕመም፣ ደም ግፊት እንዲሁም ለሌሎች ሕመሞችም የተጋለጡ ይሆናሉ እዚህ ላይ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በጦርነት በሚያጋጥም የሥነልቦና ችግር ምክንያት ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በ15 እጥፍ ራሳቸውን ለማጥፋት የተጋለጡ፤ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በአራት እጥፍ ሱሰኛ የሚሆኑበት ዕድል ሰፊ ይሆናል ይላሉ

ሌላዋ የሥነልቦና ባለሞያ ወይዘሮ ሰብለ ኃይሉ በበኩላቸው፤ ጦርነት ከሚያስከትለው ሞት ፤ የንብረት ውድመት እና የአካል ጉዳት በተጨማሪ የሚያስከትለው የስነልቦና ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ነው የጠቀሱት በዚህ ሳቢያ ተስፋ ማጣት፣ በተለይ ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድ የሞተባቸው ደግሞ የብቸኝነት ስሜት የሚፈጠርባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በሕይወታቸው ተስፋ የሚቆርጡበት አጋጣሚም ይፈጠራል ከነዋሪዎች በተጨማሪ ወታደሩም የቅርብ ጓደኛው እና ሌሎችም በቅርብ ሲሞቱ ስለሚያይ ጭንቀት ይኖርበታል፡፡

የጦርነቱ ስነልቦናዊ ጉዳት ሲነሳ ከአዋቂዎች በተጨማሪ ሕፃናት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ ሕፃናት ራሳቸውን እና አካባቢያቸውን በቅጡ በማያውቁበት ዕድሜ ይህንን ጦርነት ማስተናገዳቸው የወደፊት ሕልውናቸው ላይ አደጋ ይጋረጣል ማኅበረሰቡ ላይ ዕምነት ያጣሉ፤ «ለምን ይህ ሆነ? » ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ስለማያገኙ ምላሽ በሌላቸው ጥያቄዎች ተወጥረው ይጨነቃሉ በማለት ይናገራሉ፡፡

የማኅበራዊ ስነልቦና ባለሙያ እና የሥነልቦና አማካሪ አቶ ደምመላሽ ይበልጣል በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ጦርነት ሰዎች ከሰዎች ጋር የሚያካሂዱት ውጊያ በመሆኑ የሰዎችን አካል ብቻ ሳይሆን አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነምሕዳራዊ ጉዳዮችን ሳይቀር የሚነካ ነው ጦርነት እና ሥነልቦና የሚያያዙ ነገሮች ሲሆኑ ሰዎች በጦርነት አካላቸው ሲጎዳ ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ሲሻከር ሥነምሕዳራቸው ሲቃወስ የአዕምሮ ጤና ችግር ያጋጥማቸዋል በተለይ ባለፈው በሰሜኑ የኢትዮጵያ አካባቢ የነበረው ጦርነት ሲነሳ ንፁሐን በስፋት ሥነልቦናቸው ሊጎዳ እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡

በጦርነቱ ጊዜ አስገድዶ መድፈር፣ ሕፃናትን ለጦርነት የማሰለፍ፣ ሰዎችን በእሳት እስከማቃጠል የደረሰ የሰውን ሥነልቦና በእጅጉ የሚጎዱ ተግባራት ሲፈፀሙ እንደነበር ይታወቃል ሰዎችን ማስፈራራት፣ ብሔር ተኮር የሆነ ጥላቻ እና ማዋረድም የነዋሪውን ሥነልቦና የሚጎዳ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም የሚሉት አቶ ደምመላሽ፤ በተጨማሪ ማኅበረሰቡ በየዕለቱ የሚጠቀሙባቸው ወይም አገልግሎት የሚያገኙባቸው ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች እና የጤና ተቋማትም መፈራረሳቸው በሕዝቡ ስነልቦና ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀላል እንደማይሆን ያስረዳሉ

«አንድን ማኅበረሰብ ከአንድ ማኅበረሰብ ጋር የሚያገናኙ መንገዶች እና ድልድዮች መሰበራቸው በራሱ የአዕምሮ ጤና ችግርን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ አያጠያይቅም እንኳን ቤተሰባቸው ፊት ለፊታቸው ሲደፈር ማየት ቀርቶ፤ ከሚኖሩበት አካባቢ መፈናቀል እና መራቅ ብቻውን የስሜት ቀውስን እንደሚያስከትል እና የስሜት ቀውስ ደግሞ ወደ አዕምሮ ሕመም የሚያድግ በመሆኑ የጦርነቱ ሥነልቦናዊ ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል» ይላሉ፡፡

ብዙ ነገሮችን ማጣት እና እንደማይገኝ ማሰብ ድብርት ውስጥ መክተቱ አይቀርም አሁን ደግሞ ነገሮች እየተረጋጉ ነዋሪው ወደ ቀድሞ ስፍራው እየተመለሰ ቢሆንም፤ ከቁሳዊ መልሶ ግንባታ ባሻገር ሥነልቦናዊ ጉዳቱን ማከም እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ስጋት አለባቸው፡፡

በጦርነት ወቅት የሚያጋጥመው የሥነልቡና ቀውስ ሰፊ መሆኑን የጠቀሱት ምሑራኑ ሆኖም ግን መታከም የሚችል መሆኑን ሳይጠቁሙ አላለፉም። ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር ሳሚ ለሥነልቡና ስብራት ማከሚያ መፍትሔ ያሉትን ሲጠቁሙ፤ ለከፍተኛ የሥነልቦና ጉዳት ተጋላጮች የሆኑ ሰዎች ካለባቸው ችግር እንዲወጡ መጀመሪያ ጦርነቱ ስነልቦናዊ ጫና የፈጠረባቸው መሆኑን እንዲያውቁ እና አምነውም ችግሩን በተለያየ መንገድ እንዲከላከሉ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅመው ጉዳቱን እንዲቀንሱ ማድረግ ነው ሌላው በዚህ ጉዳይ ላይ ሙያተኛ የሆኑ ሰዎችን በማሰባሰብ በጥናት ላይ የተመረኮዘ ሥራ እንዲሠሩ ማገዝ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ሰብለ በበኩላቸው የተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር ሳሚን ሃሳብ በመጋራት በተጨማሪነት ደግሞ በጦርነቱ የፈራረሱ ትምህርት ቤቶችን መልሶ መገንባት፣ ጤና ጣቢያዎች፣ መንገዶች ፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ሆቴሎች እና ሌሎችንም መልሶ መገንባት በራሱ አካላዊ ድጋፍ ቢመስልም መልሶ መገንባቱ ሥነልቦናዊ ጥቅምም ይኖረዋል ሲሉ የመፍትሔ ሀሳብ ያሉትን አካፍለውናል።

ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ የመፍትሔ ሀሳብ ሲሉ ያቀረቡት ደግሞ እናቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና ከሁሉም በአዕምሮ ጤና በሥነልቦና ዙሪያ የሚሠሩ ባለሙያዎችን የማኅበረሰቡን ሥነልቡና በማከም ላይ ርብርብ ያስፈልጋል ሲሉ ነው የጦርነት ሥነልቦናዊ ጉዳት ቢባልም ይሔኛው እርስ በእርሳችን የደረሰ ስለሆነ ይቅርታ ማለት ባህላችን ነው ነገር ግን ሥነልቦናዊ ጉዳቱን ለመቀነስና በይቅርታ ለማከም የራሱ የሆነ ጥበብ ይፈልጋል እህት በወንድሙ ፣ ወንድም በእህቱ፤ ወላጅ በልጁ ፤ልጅ በወላጁ ላይ የተነሳበት ሁኔታ ስለነበር በጣም የሚያም በመሆኑ ብዙ ሥራ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን ተናግረዋል።

«ይሄ ጊዜ የሚፈጅ፤ በጥበብ መያዝ መካሔድ የሚገባው ጉዳይ ሲሆን፤ እኔና መሰሎቼ ብዙ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅብናል የሥነልቦና ወይም የአዕምሮ ቁስል በጣም ከባድ ነው ቁስለቱ የቅርብ ጊዜ ነው ቶሎ ወደ ይቅርታ እና እርቀሰላም መግባትን ይጠይቃል ቶሎ ወደ ንስሐ ፣ ቶሎ ወደ ካሳ መግባትን ይጠይቃል ሽምግልና ያስፈልጋል ተጎጂዎች ቁስላቸው እንዲደርቅ መደረግ አለበት መታወስ ያስፈልጋል ቶሎ ካሳ መስጠት አለበት ችግርን በሚገባ ፣ስህተትን በሚገባ አምኖ ተቀብሎ በይቅርታ መሔድ አንዱ ለአዕምሮ ቁስል መሻር የራሱን አስተዋፅ የሚበረክት መሆኑን ማስረዳት መፍትሔ ነው" ሲሉ ያብራራሉ፡፡

አቶ ደምመላሽ መፍትሔ ይሆናሉ ብለው የሚያምኑት፤ የሥነልቦና ባለሙያ፣ የአዕምሮ ጤና ባለሞያዎች፣ የማኅበራዊ ባለሙያዎችም ሆኑ የተለያዩ አካላት በጋራ በመንቀሳቀስ እና ንቅናቄ በመፍጠር በስፋት በጦርነቱ አካባቢ የነበረውን እና ያለውን የስነልቦና ጉዳት ለመቀነስ ሊሠራበት ይገባል ብለዋል።

ሌላው ደግሞ መንግሥት የራሱን ሥራ መሥራት አለበት ነገር ግን ጉዳዩ እጅግ ከባድ እና ውስብስብ በመሆኑ ለመንግሥት ብቻ ከመተው ይልቅ ግለሰቦች እና እርዳታ የሚሰጡ ተቋማት ከወደመው ንብረት በተጨማሪ የሥነልቦና ጉዳቱንም በተወሰነ መንገድ ለመቀነስ ጥረት ማድረግ እና በቅንጅት መሥራት አለባቸው የሚል እምነት እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡

«የጦርነቱ ተጎጂዎች ችግር ውስጥ የገቡት ወደው ባለመሆኑ፤ ይህንን የጦርነቱን ሥነልቦና ቁስል የሚሽርበት ሁኔታ እንዲፈጠር ቢያንስ ዛሬ ተጎጂዎች መብላት እና መጠጣት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ መሠራት አለበት የሚያድሩበት እና የሚመገቡበት ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላ በተጨማሪነት ሥነልቦናው ላይም ተመሳሳይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት እዚህ ላይ ሁሉም የየራሱን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል» ይላሉ፡፡

የአዕምሮ ጤና ጉዳቱ የራስን ሕይወት እስከማጥፋት የሚዘልቅ ሲሆን፤ ከማብላት እና ከማጠጣት ያልተናነሰ ትኩረት በመስጠት የተለያየ መፍትሔ ለማምጣት ጥረት መደረግ አለበት ለምሳሌ ያህል ማኅበራዊ ሕይወት በራሱ አንዱ የሥነልቦና ሕክምና በመሆኑ የእምነት ተቋማት አባቶች አካባቢው ከጦርነት የጭንቀት መንፈስ እንዲላቀቅን የሥነልቦና ጉዳቱ እንዲቀንስ ምዕመኑን ማረጋጋት እና ማስተማር ላይ መሥራት እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

ወታደሮችም በበኩላቸው ነገሮች እያለፉ፤ ችግሩ እየተፈታ መሆኑን በመግለፅ ሕዝቡን የማረጋጋት ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል መንግሥትም ከዕለት ደራሽ እርዳታ በተጨማሪ መሥራት ይጠበቅበታል ሁሉም በሚችለው አቅም ለተጎጂዎች አለንላችሁ ቢል በራሱ አንድ የሥነልቦና ችግሩን ማቃለል መሆኑን በመጠቆም ነገር ግን ደግሞ የኢትዮጵያ የሥነልቦና ማኅበር (የኢትዮጵያ የሳይኮሎጂ ማኅበር) የመሳሰሉ የሙያ ማኅበራት እና ሌሎችም መንግሥታዊ ያልሆኑ የሙያ ማኅበራት አባላቶቻቸውን በማነቃቃት የዘመቻ ሥራ ቢሠሩና በሚችሉት አቅም አስተባብረው ማኅበረሰቡ ጋር ደርሰው የማማከር የተጠፋፉ ቤተሰቦች የማገናኘት እና ሌሎችም መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሥራዎችን ሊሠሩ ይችላሉ የሚል እምነት እንዳላቸውም ይገልፃሉ፡፡

በመጨረሻም አቶ ደምመላሽ፤ ጉዳዩ ሰፊ ጉዳቱም እጅግ ትልቅ ስለሆነ ቀጣይነት ያለው ሥነልቡናን የማከም ሥራ መሠራት አለበት እዚህ ላይ የሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዙሪያ መሥራት የሚችሉ የገንዘብ አቅም ካላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመሥራት ችግሩን ለማቃለል ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ነው የተናገሩት፡፡

ሁሉም ምሑራን የተስማሙት ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልገው የተጎዳውን ሥነልቡና በሚያክም መልኩ በእምነት ተቋማት አባቶች ፣በታዋቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ሰፊ ሥራ መሥራት ነው ። ልክ የምግብና የመጠጥ ያህል ተጎጂዎች የሥነልቡና ሕክምና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የወደሙ መሠረተ ልማቶችን በኅብረት መልሶ መገንባት እና በይቅርታ መተላለፍን ወደፊት ማምጣት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በሁሉም ወገን ጠንካራ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

> **ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልገው የተጎዳውን ሥነልቡና ማከም ነው**

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የሺዎች እናት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ብዙዎቻችን « ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች» የሚለውን አባባል ከእናቶቻችን ማንነት ጋር ማያያዛችን የተለመደ ነው። የአብዛኞቻችን ምክያታችንም ተመሳሳይ ይመስለኛል። እናት ለቤተሰቧ ስትል የማትከፍለው ነገር እንደሌለ ለማሳየት አባባሉ ተስማሚ ነው።

አዎ እናት ስለቤተሰቧ ብዙ ትሆናለች ።አንዱና ዋንኛው ዝቅ ብላ ሰርታ ልጆቿን ከፍ ማድረጓ ነው። ሌላው ደግሞ ምንም ሳያምራት ልጆቿ የፈለጉት ነገር እንዲሟላላቸው ታደርጋለች። ሕይወቷን፣ ልጅነቷን፣ ደስታዋን ሁሉ ለእነርሱ ትሰጣለች። የእርሷ የሆነ ነገር ሁሉ የእነርሱ ብቻ እንደሆነ ታስባለች ። ‹‹ከእኔ ልጆቼ ይቅደሙ›› ማለት መለያዋ ነው።

እናት የጓዳ መብራት ብቻ አይደለችም። የተራራ ላይ ብርሀን ጭምር ናት የምንለው ለዚህ ነው። ልጆቿን በባህሪና በተስተካከለ መንገድ እየመራች ከፍታውን ታሳያለች። እንዲሆኑላት የምትሻውን ብቻ ሳይሆን እንዲሆኑ የሚፈልጉትን ለመምራት እንደሻማ ቀልጣ ያሰቡትን ታደርጋለች። በቃ ስለእሷ ለመናገር በቃላት መወሰን አይቻልም። እርሷ ስትታሰብ እርግዝና እና ሕፃናትን ተንከባክቦ ማሳደግ ትንሹ ሥራ ይሆናል ። ከዚያ ሻገር የሚለውና ብዙ ፈታኝ ነገሮች ያሉበት ሥራ ነው ለእነርሱ ብርታትና መሻገሪያቸው። በዚያ ውስጥ ሆነው የልጆቻቸውን ነገ አሻግረው ያያሉ፤ በዚያ መከራ ውስጥ ሆነው ተስፋ የሚያደርጉትን ያረጋግጣሉ። ምክንያቱም ያንን እንደሚያሳኩት አምነው ይጓዛሉና ።

ስለ እናትነት ስናነሳ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አርግዞ መውለድ ብቻ እንዳልሆነም ብዙዎቻችን የምንስማማበት ጉዳይ ነው። ምክያቱም የእናትነት ቦታ ተጨማሪነት አለበት። ሳይወልዱ የእናትን ኃላፊነት መሸከም፤ ከእናት አልፎ አባትም መሆን፤ ያልወለዱትም ማሳደግና መሰል ነገሮችን አክሎና የእኔ ነው ብሎ መስራትን ይጨምራል።

አንዳንዴ እናትነት ዘመድ ወይም የሥጋ ግንኙነት የማይተካው ሲሆንም ይታያል። ይህ ደግሞ እናትነት ከሴትም በላይ ተጨማሪ ተፈጥሯዊ ስጦታ እንደሆነ ይነግረናል።

ወደ ሥራው አለም ስንገባም ይህንኑ ነው የምናረጋግጠው። እናትነት ለማንኛውም ተልዕኮ በቂነት እንደሆነ። ጾታ፤ እድሜ የማይገድበው ትህትና። ለዚህም በማሳያነት የምናነሳው እያንዳንዱ ቀን ለልጆቼ በሚል የተከፋፈለና ያለ እረፍት የሚለፋበት መሆኑን ነው። እናት ዘወትር በቀኗ ውስጥ የምታደርገውን ነገሮች እንዳለ ለልጆቿ ለውጥ የሚውል መሆኑ። ከቤት ህይወት ብንነሳ እንኳን ልጆቿን አጥባ ማሳመር መነሻዋ ነው።

ሲርባቸው መመገብ፣ ሲደክማቸው ማስተኛት፣ የተዘበራረቀውን ማስተካከል፣ የቆሸሹትን ልብሶች ማጠብ፣ የከፋቸውን ልጆች ማጽናናት ፤ ባዶ የሆነውን መሶብ መሙላት፣ ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል ። ይህን ሀላፊነት ስትጨርስ ደግሞ ከውጭ የሚጠብቃትን ሥራ ትቀጥላለች።

ሁሉንም ቤተሰብ በቤት ውስጥ ደስተኛ የምታደርገው ከቤት አልፋ ውጪም ላይ ሰርታ በምታመጣው ገንዘብ እንደሆነ ይታወቃል። እናም ልክ እንደወንዱ እኩል ለፍታ ቤቷን ሙሉ ለማድረግ የቤቱን ሥራ አጠናቃ ትወጣለች። ትንሽ ከትልቅ የሚባለውን ሁሉ ትሰራለች። ዋና አላማዋ ልጆቿን የሚደጉምላት ገቢ ማግኘቷ ላይ ነው።

የውጩን ልፋት ፤ የቤቱን ችግር ለመፍታት ታትራ ትሰራለች። ቤቷ ስትገባ ፈገግታ የሚሞላትም ይህ ነገሯ ሲሳካላት ነው። በዚያው ልክ ቤቱ ሳይሞላላት ሲቀር ደግሞ የምታለቅስና ምን ላጉርሳቸው እያለች የምትጨነቅም እናት ትኖራለች ።

ሥራ ማግኘቱ፤ የኑሮ ውድነቱ፤ የቤት ኪራዩና መሰል ጉዳዮች ከራሳቸው አልፎ ቤተሰባቸውን የፈተነባቸው እናቶች ቁጥር ቀላል አይደለም። ከእነዚህ መካከል ለዛሬ ልናነሳቸው የወደድናቸው መጋቢ እናቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እናቶቹ ሥራ አላቸው ቢባልም የሚያገኙት ገቢ ግን ኑሯቸውን የሚደጉምና ከፍ ሊያደርጋቸው የሚችል እንዳልሆነ በአንደበታቸው ይናገራሉ።

መንግስት በፈጠረው የተማሪዎች ምገባ ሥራ ላይ በመሰማራታቸው በመጠኑ ችግሮቻቸው እንደተቀረፈ ግን አይሸሽጉም ። ከራሳቸው ልጅ አልፈው ለሌሎች የሚደርሱ መሆናቸው ደስታን ቢፈጥርላቸውም ደስታው



ወይዘሮ አይናለም ጉልላት

የሚደምቀው ግን ጎዶሏቸው ሲሞላ እንደሆነ ያነሳሉ። ለሥራው የሚመጥን ገንዘብ ማግኘት ቢታከልበት በሚል።

እነዚህ እናቶች ጉዳያቸውን መንግስት በአግባቡ ሊያይላቸው እንደሚገባ አንስተውልናል። ወይዘሮ አይናለም ጉልላት ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ ብቻቸውን አምስት ልጆች አሳድገዋል። ልጆቻቸውን ለማሳደግ እሞክረዋለሁ ብለው የማያስቡትን ሥራ ጭምር ሰርተዋል። የሰው ቤት ጠርገዋል፤ ልብስ አጥበዋል፤ በአጠቃላይ የቀን ሰራተኛ ሆነዋል። ሁሌ በማህበረሰቡ ዘንድ ትንንሽ በሚባሉ ሥራዎች ለመገኘት ወደኋላ ብለው አያውቁም።በዚህም ኑሯቸውን በመለወጥ ቤት ጓዳቸውን ሞልተዋል ።

ለእናቶች የሥራ ፋክክር ይሉት ጉዳይ ቦታ የለውም። ሁልጊዜም ጥረታቸው ያለፉክክር ቤታቸውን እንዴት መሙላት እንደሚችሉ ነው። ደፋ ቀና ሲሉም ለዚህ ሁሉ ችግራቸው መፍትሄ በመስጠት ውስጥ እያለፉ ነው። ሁሉን በስርአት እየመሩ፣ የቻሉትን ያህል እየደከሙ፣ ቤቱ ሙሉ ባይሆንም ጎዶሎውን ይደፍናሉ። ቤት በብልሀት ሲገነባ የማይሞላ አይኖርምና አሁንም በዚህ የትጋት መስመር እያለፉ መሆኑን ይናገራሉ ፡፡

እንደርሳቸው እምነት ርቀትን ጠብቆ ፣ ፍጥነትን ገድቦ ለመብረር የድካም ዋጋ መክፈል ግድ ነው። መልካም አጋጣሚዎች የሚገኙት ደግሞ በዚህ ልክ መልፋት ሲቻል ነው ። እናቶች ከምንም በላይ ትጉህነታቸው የሚቀድም የመሆኑ ምስጢርም ሌላ ሚስጥር የለውም ።ሁሌም በትጋት ውስጥ ወርቃማ ውጤት ይገኛል ብለው ያስባሉ ።

ስለዚህም ትጋትን መመሪያቸው፤ መታወቂያቸው፣ ብርታትና ከበሬታቸው አድርገው ይጓዙበታል። በዚህ ደግሞ ያሰቡት ላይ ይደርሳሉ ።

ምንም እንኳን በአጋሮችና በዘመድ ድጋፍ ኃላፊነታቸው ቢቀልም ከእነርሱ ውጪ የሚደረግ ነገር ደስተኛ አያደርጋቸውም። በዚህም ቤታችን ያለእኛ አስተዳደር ሙሉ አይሆንም በሚል ቀን አልፎ ቀን እስኪተካ ይለፋሉ። እፎይ የሚሉትን ነገር አያስቡትም የሚል አመለካከት ያላቸው ወይዘሮ አይናለም፤ በሥራቸው ውስጥ ልጆቻቸውን እያዩ በተስፋ ፈረስ መጋለብ ነው የእርሳቸው ስኬትና የዛሬ ጉዟቸው ውጤት። እናም ለሁሉም ልጆቻቸው የሚመቹ መሆናቸውን እያረጋገጡ ይጓዛሉ።

እንደ ተፈጠሩለት አላማ አድርገው ለባላቸው ፤ ለልጆቻቸው ምቹ መሆንን ያውቁበታልና ባለቤታቸውን በሞት ቢነጠቁም ለልጆቻቸው ብለው ይኖራሉ። ዕድሜያቸውን ሙሉ መልካም ማድረግን ባህሪያቸው አድርገው ለልጆቻቸው አልፎ ተርፎ ለቤተሰብና ለጎረቤታቸው ተምሳሌት እየሆኑም ይገኛሉ። መልካምነታቸው በጊዜና ሁኔታ፣ በማግኘት በማጣት አይገደብም። ምክንያቱም ሁሉንም የሚያዩበት ዓይን የልጅነትና የእናትነት ነውና።

እናትነት ፈተናን ለልጆች ሲባል መጋፈጥ እንደሆነ ያውቃሉና የሚሰጡትን አጋጣሚዎች ሁሉ ይጠቀማሉ። አንደኛው ማሳያ ወደ ምገባ ሥራ የገቡበት አጋጣሚ ነው። ሥራውን የጀመሩት ከዛሬ ሰባትና ስምንት ዓመት በፊት ነበር። በአካባቢያቸው « የእናት ወግ» በተሰኘና የተመረጡ ችግረኛ እናቶችን በያዘ ስብስብ የሥራ



ወይዘሮ ዘነበች ተክሉ

አማራጭ የሚያገኙበት ሁኔታ ነበርና በዚያ ውስጥ ተመልምለው ትምህርትቤት ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎችን እንዲመግቡ ተደርገዋል። ይህ ደግሞ ቢያንስ ልጆቻቸው በልተው እንዲያድሩ አስችሏቸዋል። ከሙሉ ጊዜ የቀን ሰራተኝነትም በመጠኑ ላቋቸዋል።

አሁን ደግሞ ሁሉም ተማሪ ይመገብ ሲባል የመስራት አቅማቸው ጨምሯል። ልጆቻቸውን በቤታቸው እንደሚያጎርሱ እናቶች ሆነው ጥራት ያለው ምግብ በማዘጋጀት መመገብ ጀምረዋል ። በእርግጥ በዚህም ቢሆን ፈተናው ቀላል አልሆነላቸውም ። ለተማሪዎቹ ሲባል ሁሉንም በቤታቸው ያዘጋጃሉና ክፍያውና የሚያወጡት ወጪ እንዲሁም የልፋታቸው ነገር ተመጣጣኝ አይደለም።

ወይዘሮ አይናለም እንደሚሉት፤ እናቶች ከእነርሱ የባሱ ሰዎች ካዩ አያስችላቸውም። መስጠትን ልምድ አድርገውታል ። እጃቸውን ወደ ድሀ መዘርጋት ባህሪያቸው ነው። መልካም እናት ስጦታዋ እንካ በእንካ ነውና በአፀፋዉ የምትጠብቀዉ የለም። ‹‹አድርጌያለሁ›› የሚል አስተሳሰብም አይንጸባረቅባትም። ወረታዋን በልጆቿ ደስታ አለያም ሰርቶ በመለወጥ እንደምታገኘው ታምናለች። ይህንን ሥራዋንም በራሷ ደስታ ትመነዝረዋለች። ወይዘሮዋም ለዚህ ማሳያ እንዲህ ይላሉ። « ብዙ ችግሮች ገጥመውኝ መፍትሄ ሲሆኑኝ አይቻለሁ። አንዱና ዛሬ ድረስ የማልረሳው ለልጆቼ የምመግበው አጥቼ የለመንኩትና አንድ እፍኝ ሩዝ ያገኘሁበት ነው»

በአሁኑ ጊዜ ሁሉም በቤቱ የኑሮ ውድነቱ በገባበት ሰዓት እንኳን ተጋርቶ መብላት በሁሉም ዘንድ አለ የሚሉት ወይዘሮ አይናለም፤ የቀን ሰራተኛ እያሉም ሆነ አሁን በምገባው ላይ ተሰማርተው ባሉበት ወቅት በምግብ ጉዳይ አይመለከተኝም የሚል እንደማይኖር ያነሳሉ ።

ቀና አድርጎ ውሃ ማጠጣት ብቻ ሳይሆን ምግብ ማብላትም በሁሉም ማህበረሰባችን ዘንድ ልምድ ብቻ ሳይሆን የአዕምሮም እርካታ ነው። እናም እኛ በምገባው ዙሪያ ያልተቸገርነው ለዚህ ነው ይላሉ ። ይሁን እንጂ አሁን ላይ አንድ ነገር እንደሚያሳስባቸው አልሸሸጉንም። ይህም የሚመጣው ገንዘብ የልጆቻቸውን የትምህርት ወጪ የሚሸፍን አለመሆኑን ነው።

መንግስት የደንብ ልብስና ደብተር፣ እስኪርብቶ ፣ መስጠቱ ትንሽ እፎይታን እንደሰጣቸው የሚያነሱት ባለታሪካችን፤ ወጪው በዚህ ብቻ የሚያበቃ ስላልሆነ እጅግ እየተፈተኑ እንደሆነ ያስረዳሉ። በተለይም ሁለተኛ ደረጃ ላይ የገባ ልጅ ስላላቸው ምገባው በዚያ አለመድረሱ፤ ተጨማሪ አጋዥ መጻሐፍትና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶች ለምትማረው ልጃቸው ማስፈለጉ እርሳቸው ከሚያገኙት ገቢ ጋር አለመጣጣሙ፤ የቤት ኪራይና የማገዶ ወጪዎችም ቢሆኑ ለእርሳቸው ፈተና ናቸው። እናም ሁልጊዜ ጭንቀት ውስጥ ሲሆኑ፤ ደጋግመው

ምን ላድርግ ? እንደሚሉ ነግረውናል።

በቀደመው ኑሯቸው ቤታቸውን ሙሉ ለማድረግ የሚጥሩት ባለቤታቸው ነበሩ። እሳቸውም ቢሆኑ በቀን ሰራተኛነት በግንበኝነትና ለሳኝነት ላባቸውን ጠብ አድርገው በሚያመጡት ገንዘብ ደስተኛ ቤተሰብን ሲፈጥሩ ቆይተዋል። ሆኖም ሞት አይቀሬ ሆኖ እስከወዲያኛው በመለየት ተሰናበታቸው ።

ከጊዜ በኋላ የአባወራውን ቦታ ተክቶ ለልጆቻቸው ደስታ መኖር የእርሳቸው ኃላፊነት ሆነ ። እናም ልጆቻቸውን ለማኖር የቻሉትን እያደረጉ ዛሬ ድረስ ዘለቁ። በዚህ አጋጣሚ ልጆች ሥራ ወዳድ ሆነው አድገዋል።

ትንንሾቹ የቤት ሥራ ሲያግዙ ትልቋና ዘንድሮ 12ኛ ክፍል የተፈተነችው ልጃቸው የፋብሪካ ሥራ በመስራት ከራሷ አልፋ ቤቱን የመደጎም ተግባርን እንድታከናውን ሆናለች።

እርሷ ባትኖር ኖሮ በቤት ኪራዩ ጭማሪ ኑሮን መቋቋም እንደማይችሉ ያጫወቱን ወይዘሮ አይናለም፤ ዛሬ በትንሹም ቢሆን ‹‹እፎይ›› የማለታቸው ምስጢር ልጃቸው እንደሆነች ይናገራሉ። የራሷን የትምህርት ቤት ወጪ በራሷ ሸፍና ለእናቷ መቀነት የቡና ማለት ችላለችና ሁልጊዜ ይመርቋታል።

እንደ ወይዘሮ አይናለም ሁሉ ወይዘሮ ዘነበች ኃይሌም በብዙ ፈተናዎች ያለፉ ሴት ናቸው ። አሁንም ብዙ ችግሮቻቸው መፍትሄ እያገኙላቸው እንዳልሆነ ይናገራሉ። በተለይ የራስ ሥራ መፍጠር ላይ ብዙ ችግሮች እያጋጠሟቸው መሆኑን ያስረዳሉ። ሁልጊዜም በምገባው ላይ መስራት ለሌላው ችግረኛ ቤተሰብ ቦታ አለመልቀቅ እንደሆነ ያስባሉ። በብዙዎች ዘንድ ምገባ ላይ መስራት ትርፋማ እንደሆነ ይታሰባል። ሆኖም በተለይም እንደእነርሱ ያሉ ሴቶች በዚህ ዘርፍ ላይ ብቻ ተወስኖ መስራት ከትርፉ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንም ያስረዳሉ። በምክንያትነት የሚያነሱትም ወጣት ሲኮን ብዙ መልፋትና መሥራት እንደሆነ ማመናቸው ነው።

አሁን ባለንበት ሁኔታ ‹‹አጣሁኝ ›› ማለት አይቻልም ። ነገር ግን ቋሚ ሥራ ያስፈልገናል ። ኑሮ በጣም ተወዷል። በምገባ የምንሞላው ነገር እንደ አንድ ገቢ ቢወሰድም ከዚያ ውጪ ያሉ ወጪዎች ግን የበረከቱ መሆናቸው አጣጥሞ ለመጓዝ ፈተና ሆኗል።

እንደሳቸው ዕምነት በመንግስት ብድር ተፈቅዶላቸው ሌላ ተጨማሪ ሥራ አለያም በስፋት የሚንቀሳቀስበት የሥራ መስክ ቢፈጠር የተሻለ ይሆናል። እንዲህ ማድረግ ከተቻለ ውጤታማ ለመሆን አማራጩ ይሰፋል። በተጨማሪም ለሌሎች የሥራ እድሉን ለመፍጠርም አቅም ይኖረናል ይላሉ።

ጠንካራዎቹ እናቶች ዘመኑን የሚዋጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል ። ባለፉት ችግራቸው እየሳቁ ፣በአዲሱ ኑሯቸው ደስታን ለማምጣት ሊተጉም ይገባል። ኋለኛዉ ዘመን አልፏል። ያለፈውን ችግር እያሰቡ በትዝታ እየቆዘሙ እንዲጓዙ ለራሳቸው መፈቀድ የለባቸውም ።

የቆሙበት ዘመን ሳያስፈራቸው ኑሮን ድል የሚያደርጉበት መንገድ እንዲፈጠር ከመንግስትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ ሊኖር ያስፈልገናል። ይህ ሀሳብ የሁሉም እናቶች ውስጣዊ ስሜት ነው ።

ሴቶች የሚመሩት ቤተሰብ ሲኖራቸው ቀድመው መዘጋጀትና ለወደፊቱ መደላደልን መፍጠር ግዴታቸው እንደሆነ የሚያነሱት ወይዘሮ ዘነበች፤ ከባለቤታቸው ጋር አብረው መኖር ስላልቻሉ ሦስቱንም ልጆቻቸውን ራሳቸው ለማስተዳደር ወስነው ቀን ከሌት እየለፉ ነው። ይህንን ደግሞ በተሻለ ሥራ መደገፍ ካልቻሉ ነገሮች እንደሚከብዱባቸው ያውቃሉና አሰራርን በማስተካከል መንግስት ቢያግዘን ይላሉ።

ብርቱዎቹ እናቶች የታወቁ ባለሙያም ናቸው ። በእጆቻቸው ፍሬ የማያጠግቡት የለም። የሚል እምነት ያላቸው ወይዘሮ ዘነበች፤ በሙያቸው የውስጡንም የውጪውንም አለም ያጣፍጣሉ። ያላቸውን አቅም ተጠቅመው በማስተዳደር ብቃትታቸውን ማስመስከርም ይችላሉ። የሌለውን ፈጥሮ የማቅረብና ከቤት አልፈው ለውጪ ግርማ ሞገስ ይሆናሉ። መፍትሄ አምጪም ናቸው።

እነዚህን እውነታዎች ተገንዝቦ ትኩረት ቢደረግ የሚል አስተያየት ያላቸው ወይዘሮ ከቀበሌ ብድር ይሰጣችኋል ተብለው ምገባ ላይ ስለሚሰሩ ብቻ አትችሉም መባላቸው እንዳሳዘናቸው ይገልጻሉ። የሚመለከተው አካልም ለጉዳዩ መፍትሄ ሊቸራቸው እንደሚሹም አጫውተውናል።

ወይዘሮ ዘነበች መንግስትን አመስግነው አይጠግቡም። መንግስት ምንም የስራ ዕድል በሌለበት ሁኔታ እርሳቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ በሩን ከፍት አድርጎላቸዋል። ልጆቻቸውም ቢሆኑ በትምህርትቤቱ ዕድል ተመጋቢ ስለሆኑ እፎይታን አግኝተዋል። ለዚህም ዘወትር ምስጋናን ይቸራሉ። ከዚያ ባሻገር ግን እንደ አንዲት ሴት ሥራዎቿ በሸንጎ፣ ልጆቿ በአደባባይ የሚያደንቋት መሆንን ይሻሉና ብድሩ የሚፈቀድበት አጋጣሚ ካለ ቢመቻችልኝ ይላሉ። እኛም በምገባው ዙሪያ ያሉ እናቶች ደሞዝና ችግሮቻቸው ቢፈቱላቸው በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን። ሰላም!!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በሀገር መከላከያ ሠራዊት ሰሜን ዕዝ ላይ የተፈፀመው ክህደትና ሠራዊቱ የተጨፈጨፈበት ሁለተኛ ዓመት ባለፈው ጥቅምት 24 በልዩ ሁኔታ ታስቦ መዋሉ ይታወሳል፡፡ የተፈፀመው ግፍ ሁለተኛ ዓመት በሚታሰብበት ዋዜማ መንግሥት ከሕውሓት ጋር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በናጄሪያው የቀድሞው መሪ ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆ አማካኝነት የሰላም ውይይት አካሂዶ ሕውሓት ጦሩን ሊያወርድ፣ በሀገሪቱም ሰላምን ለማስፈን ተስማምቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያ በተመድ ጉባዔ የዛሬ ሃምሳ ዓመት በናይጄሪያ ቢያፍራ የነበረውን ጦርነት ለማብረድና ዕርቅ ለማውረድ ጥረት እያደረገች መሆኑ በጋዜጣችን ተዘግቦ ነበር፡፡በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችንን ያንን ታሪክ የሚያስታውሰንን ዘገባ መለስ ብለን እንቃኛለን፡፡ በተጨማሪም በዚያ ወቅት አንድ ለማኝ ሞተው በማሰሮ 430 ብር ስለመገኘቱ በጋዜጣው ተዘግቦ የነበረን ክስተት አካተናል፡፡ መቼም ይህ ክስተት በዜና የተዘገበው በወቅቱ 430 ብር ትልቅ ዋጋ ስለነበረው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሐረር አጭር ቀሚስ በለበሱ ላይ በፖሊስ ስለሚደረገው ቁጥጥር እና ሌሎችም ዜናዎችንም አካተን እነሆ ብለናል፡፡

### በናይጄሪያ ውስጥ ሰላም እንዲገኝ ኢትዮጵያ ትጥራለች -ከተማ ይፍሩ በተባበሩት መንግሥታት ጉባዔ

ከተባበሩት መንግሥታት፤(ሮይተር) ኢትዮጵያ የናይጄሪያን የርስ በርስ ጦርነት ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት እንዲቀጥል አሳሰበች፡፡

ማሳሰቢያውን ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ያቀረቡት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ናቸው፡ ፡ ክቡርነታቸው በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ሊቀመንበርነት የሚመራው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የናይጄሪያ አስታራቂ ኮሚቴ ፤ጦርነቱን ለማቆም ከፍ ያለ ጥረት ማድረጉን ገልጠዋል፡፡

ክቡር አቶ ከተማ መንግሥታቸው ይህ አሳዛኝ ዕልቂት በሰላማዊ መንገድ ፍጻሜ እንዲያገኝ የሚያደርገውን ጥረት የማያቋርጥ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ክቡር አቶ ከተማ፤ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያለውን ልዩነት ለማስወገድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በቂ እርምጃ ስላልወሰደ ፤ ወደፊት ይህን አጉል እምነት ለማገድ በቂ የሆነ እርምጃ እንዲወስድ ጠይቀዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታትድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተገኙትን የኢትዮጵያ መልእክተኞች የሚመሩት አቶ ከተማ ይፍሩ ፤በደቡብ አፍሪካና በሮዴዚያ ውስጥ ያሉት የጥቂት ነጮች መንግሥታት፤ሥፍራዎቻቸውን ለይበልጡ ጥቁር አፍሪካውያን ሕዝብ መንግሥታት እንዲለቁ በጉዳዩ ኃያላን ሀገሮች እንዲተባበሩ አሳስበዋል፡፡ፖርቱጋልም ሕገወጥ ሥልጣኗን መከታ በማድረግ በአፍሪካውያን ላይ የምትፈጽመውን በደል እንድታቆም መጠየቃቸው ታውቋል፡፡ክቡር ሚኒስትሩ ስለ አፍሪካ ጉዳዮች ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከዊሊያም ሮጀርስ ጋር ተነጋግረዋል፡፡

**( መስከረም 29 ቀን 1962 ከወጣው አዲስ ዘመን )**

### ለማኙ አቶ ወልደማርያም ሞቱ ከራስጌያቸው ማሰሮ 430 ብር ተቀብሮ !

አሰበ ተፈሪ ፡-(ኢ-ዜ-አ-) በሐረርጌ ጠቅላ ግዛት በጨርጨር አውራጃ በዶባ ወረዳ በልመና ይተዳደሩ የነበሩትና በሕመም ሞት ባለፈው ጳጉሜ ፫ ቀን ፲፱ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩት በአቶ ወልደ ማርያም መኖሪያ ጐጆ ውስጥ በማሰሮ የተቀመጠ ፬፻፴፫ ብር ከ፺ ሳንቲም መገኘቱን የወረዳው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

በልመና ይተዳደሩ የነበሩት እኚሁ አቶ ወልደማርያም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ ወዲህ ይኖሩባት የነበረችው አነስተኛ ጐጆ ሳትከፈት ቆይታ ነበር፡፡ሁኔታውን ለማጣራት የወረዳው ገዢ ፤የወረዳው ፖሊስ ረዳት አዛዥና የሀገር ሽማግሌዎች በተገኙበት ሰሞኑን ጐጆዋ ተከፍታ ስትፈተሽ በሟቹ ራስጌ በነበረው ማሰሮ ፬፻፴፫ ብር ከ፺ ሳንቲም ሊገኝ ችሏል፡፡ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ፪፻፺፩ ብር ከ፶ ሳንቲም ነጭ ሽልንግ ፤፹ ብር ከ፳፭ ሳንቲም ባለ ሃያ አምስት ሳንቲም መሆኑ ተገልጧል፡፡

ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ለከሰል ፲፭ ብር ከ፸፭ ሳንቲም ወጪ ሲሆን ፤ተራፊውንም ፬፻፲፰ ብር ከ፲፭ ሳንቲም የዶባ ወረዳ ግዛት ፖሊስ ጽሕፈት ቤት መረከቡ ተረጋግጧል፡፡

ስለዚህ የሟች ወራሽ ወይም ተወላጅ የሆነ ሰው ማስረጃውን አቅርቦ ገንዘቡን ለመረከብ መቻሉን የአውራጃው ፖሊስ መምሪያ አስታውቋል ፡፡

**( መስከረም 29 ቀን 1962 ከወጣው አዲስ ዘመን )**

### የአጭር ቀሚስ ቁጥጥር በሐረር

ሐረር፡ (ኢ-ዜ-አ-) በሐረር ከተማ ውስጥ አጫጭር ቀሚስ እየለበሱ በሚዘዋወሩት ሴቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን የሐረር አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ ገለጡ፡፡

በተደረገው ቁጥጥር መሠረት በሐረር ከተማ ውስጥ የሀገርን ባህል የሚያጎድፍ ልብስ ለብሰው የተገኙት ፳፯ ልጃገረዶችና ሴቶች ፪ኛ ፖሊስ ጣቢያ እየቀረቡ ዳግመኛ ላለመልበስ መፈረማቸውን ሌተናል ኮሎኔል ኃይለ ሚካኤል አስረድተዋል፡፡

ይኸው አፈጻጸም ለወደፊቱ በየጣቢያው ተላልፎ በሚገባ በሥራ ላይ እንደሚውል ታውቋል፡፡

በዚሁ ይዞታ በከተማው ውስጥ ይታይ ነበረው የአጭር ቀሚስ ለባሾች ቁጥር መቀነሱንና ለወደፊት ጨርሶ እንደሚጠፋ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ እምነታቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡

**( ጥቅምት 2 ቀን 1962 ከወጣው አዲስ ዘመን )**

### የድኩላ ሥጋ ሰው ገደለ አሥሩ በጠና ታመዋል

ነቀምቴ፤(ኢ-ዜ-አ-) በወጥመድ ተይዞ የተገደለ የድኩላ ሥጋ በተመገቡ የአንድ ቤተሰብ አባል በሆኑ አሥራ አንድ ሰዎች ላይ የሞትና ጤና ጉዳት መድረሱ ተገለጠ፡፡ ቡልቻ ቶኬ የተባለ ሰው መስከረም ፳፪ ቀን ፷፪ ዓ-ም - አንድ ድኩላ በወጥመድ ይዞ ከገደለ በኋላ ወደ ቤት ወስዶ አሥራ አንዱም ቤተ ሰቦች ሥጋውን መመገብ ጀመሩ፡፡በዚሁ ጊዜ ከመካከላቸው ቡርሜሣ ወዳጆ ይባል የነበረው ወዲያውኑ ታምሞ ሲሞት ፤ የቀሩት ዐስሩ ሰዎች በጠና ታምመው በሕክምና ላይ ይገኛሉ፡፡


የድኩላው ሥጋ በመመገብ የሞትና በጤና ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በወለጋ ጠቅላይ ግዛት በቄለም አውራጃ የአንሲሎ ወረዳ ኗሪ መሆናቸው ታውቋል፡፡

**(ጥቅምት 6 ቀን 1962 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## በአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ የትራምፕና ባይደን የእሰጥ አገባ ቅስቀሳ





የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን እና ቀዳሚያቸው ዶናልድ ትራምፕ በተለያዩ ግዛቶች በቅስቀሳ ተጠምደዋል።ባይደንና ትራምፕ በየፊናቸው መራጮችን 'ከፊታችሁ አደጋ አለ፤ እኛን ካልመረጣችሁ' ሲሉ ቀስቅሰዋል።በአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ የሚደረገው በኅዳር ወር አዲስ ፕሬዝዳንት ወይም ለሁለተኛ ዘመን የተመረጠ ፕሬዝዳንት ነጩ ቤተ መንግሥት በገባ በ2ኛ ዓመቱ ላይ ነው።

በዚህ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ በተጓደሉና ዘመናቸውን በጨረሱ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤትና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ይደረጋል።በአጋማሽ ዘመን ምርጫ ለሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት የሚሟያ ምርጫ ብቻም ሳይሆን የግዛት አቃቢያን ሕግ፣ አስተዳዳሪዎች፣ ተወካዮች ወዘተ ምርጫዎች አብረው ይደረጋሉ።የዘንድሮ ምርጫ ከረዥም ዓመታት በኋላ ከፍተኛ ውጥረት የነገሰበት ነው ተብሏል።

በተለይም ዲሞክራቶች በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ያላቸውን የአንድ ድምጽ የበላይነት ጨርሶውኑ ያጣሉ የሚል ስጋት አድሯል።የሕግ መወሰኛው ብቻም ሳይሆን የሕግ መምሪያው ምክር ቤትም ቢሆን አሁን ሪፐብሊካኖች ይቆጣጠሩታል የሚለው ፍርሃት/ተስፋ በስፋት እየተሰማ ነው። የሕዝብ አስተያየት መለኪያዎች የሚያሳዩትም ይህንኑ ነው።

ሪፐብሊካኖች አንዱን ምክር ቤት ከተቆጣጠሩት ጆ ባይደን ደንቦችንና ሕጎችን ለማጽደቅ ከዚህ ወዲያ ፈተና ይሆንባቸዋል። ትናንት ሰኞ የምርጫ ቅስቀሳው የመጨረሻ ቀን ነው።ጆ ባይደን ትናንት በኒው ዮርክ ከተማ ገዥ ለመሆን ለሚወዳደሩት ካቲ ሆቹል የቅስቀሳ ንግግር አድርገዋል። በኒው ዮርክ የትራምፕ ወዳጅ ሊ ዘልዲን ጥሩ ተፎካካሪ ሆነው ቀርበዋል።

ካቲ ከቀድሞው ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን፣ ከምክትል ፕሬዝዳንት ካማላ ሐሪስ እና ከቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሒላሪ ክሊንተን የቅስቀሳ ድጋፍ አግኝተዋል።በዘንድሮ አጋማሽ ዘመን ምርጫ ከዚህ ቀደም ዲሞክራቶች በቀላሉ ያለምንም ውጣ ውረድ ድምጽ የሚያገኙባቸው ግዛቶች ሳይቀሩ ፊታቸውን አዙረውባቸዋል። ብዙዎቹ የቅስቀሳ ንግግሮች መራጮችን በማስጠንቀቅ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

ጆ ባይደን በአንድ የቅስቀሳ ንግግራቸው ይህ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ አሜሪካ ለሚቀጥሉት 20 ዓመታት ምን እንደምትመስል የሚወሰንበት ይሆናል፤ ልብ አድርጉ!' ብለዋል። ጨምረውም፣ ሁለት ፍጹም የማትመሳሰል የአሜሪካ ገጽታዎች ለምርጫ ቀርበዋል፤ የምትመርጡትን ከወዲሁ እወቁበት ሲሉ አስጠንቅቀዋል። ዶናልድ ትራምፕ በማያሚ ባደረጉት ቅስቀሳ ደግሞ 'ይሄ ጆ ባይደን አሜሪካንን ኮሚኒስት አገር አደረጋት' ሲሉ ከሰዋል።

የዶናልድ ትራምፕ የማያሚ ቅስቀሳ ለአንድ ሰዓት የዘለቀ ነበር። 'ዲሞክራቶች አሜሪካንን እንደ ቬንዝዌላና ኩባ ሊያደርጓት ይሻሉ' ሲሉም ተናግረዋል ዶናልድ ትራምፕ። ዶናልድ ትራምፕ በፈረንጆች 2024 ወደ ሥልጣን ለመመለስ እንዳሰቡ ፍንጭ ሰጥተዋል ትናንት ኦሃዮ ላይ በነበራቸው የቅስቀሳ ንግግር።

ዶናልድ ትራምፕ በድጋሚ ለፕሬዝዳንትነት ከተወዳደሩ የመመረጥ ሰፊ እድል እንዳላቸው ይነገራል። የሕዝብ አስተያየቶች እንደሚያሳዩት አሁን ባለው ሁኔታ ዲሞክራቶች በሕግ መምሪያው ምክር ቤት የሚኖራቸውን የበላይነት ለሪፐብሊካኖች ማስረካባቸው አይቀርም።

በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ደግሞ ማን የበላይነቱን ይይዛል የሚለው ከፍተኛ ፉክክር ይታይባቸዋል ተብለው በሚጠበቁት ሦስት ግዛቶች ማለትም በፔኒሲልቬኒያ፣ በጆርጂያ እና ኔቫዳ ምርጫ ውጤቶች ይወሰናል።ላለፉት ሁለት ዓመታት ዲሞክራቶችና ሪፐብሊካኖች በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ያላቸው መቀመጫ እኩል 50-50 ቢሆንም የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ምክትል ፕሬዝዳንት ካሚላ ሐሪስ ስለሆኑ ዲሞክራቶች በአንድ ድምጽ የበላይነት ነበራቸው።

እስከ አሁን 40 ሚሊዮን አሜሪካዊያን በፖስታ ድምጽ ሰጥተዋል። ሰኞ አሜሪካ ሲነጋላት ባይደን በሜሪላንድ የመጨረሻ ቅስቀሳ ያደርጋሉ።ማምሻ ላይ ደግሞ ዶናልድ ትራምፕ በኦሃዮ ለጄዲ ቫንስ የቅስቀሳ ድጋፍ ይሰጣሉ።ቀዳማዊት እመቤት ጂል ባይደን ወደ ቨርጂኒያ አቅንተው ለእንደራሴ ጄኔፈር ዌክስተን ድጋፋቸውን ይሰጣሉ።

የዘንድሮ አጋማሽ ምርጫ ዋንኛ አጀንዳዎች የኑሮ መወደድ፣ የነዳጅ ዋጋ ንረት፣ ወንጀል መበራከት፣ ውርጃ፣ እና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት አደጋ ላይ መውደቅ ናቸው።ዲሞክራቶች በተደጋጋሚ ትራምፕን መሰል ሰዎች ሥልጣን ከያዙ የአሜሪካ ዲሞክራሲ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይቀለበሳል ሲሉ በተደጋጋሚ ያስፈራራሉ ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ወጣት ቡድን ወደ አፍሪካ ዋንጫ ስማስፍ ዛሬ ደቡብ ሱዳንን ይገጥማል

ቦጋለ አበበ

በሱዳን አስተናጋጅነት እየተካሄደ የሚገኘው የመካከለኛውና ምሥራቅ አፍሪካ(ሴካፋ) ከ20 ዓመት በታች የእግር ኳስ ውድድር የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚዎች ከቀናት በፊት ተለይተዋል። በውድድሩ እየተካፈለ የሚገኘው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድንም የምድብ ጨዋታውን ቀዳሚ ሆኖ በማጠናቀቅ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ መሆኑን ከትናንት በስቲያ አረጋግጧል።

በውድድሩ ምድብ ሁለት ላይ ከታንዛኒያና ዩጋንዳ አቻው ጋር የተደለደለው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ባለፈው ሳምንት የመጀመሪያ ጨዋታውን አድርጎ በአቻ ውጤት ማጠናቀቁ የሚታወስ ሲሆን ሁለተኛ የምድብ ፍልሚያውን በድል በመወጣቱ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ ሆኗል።

በቅርቡ የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ሆነው በተሾሙት እድሉ ደረጀ የሚመራው የኢትዮጵያ ወጣት ብሔራዊ ቡድን በመጀመሪያው የምድብ ጨዋታ ታንዛኒያን ገጥሞ ሁለት ጊዜ ከመመራት ተነስቶ ነጥብ ተጋርቶ መውጣቱ ይታወሳል።

በጨዋታው የተሻለ የኳስ ቁጥጥር በማድረግና ዕድሎችን በመፍጠር የተሻሉ የነበሩት ታንዛኒያዎች ነበሩ። የእንቅስቃሴ ብልጫቸው ፍሬ አፍርቶም 21ኛው ደቂቃ ላይ ዲክሰን ቫላንቲኖ ባስቆጠራት ጎል ቀዳሚ መሆን ችለዋል። ሆኖም የታንዛኒያዎች መሪነት ለ10 ደቂቃዎች ብቻ የዘለቀ ነበር። 31ኛው ደቂቃ ላይ ዘላለም አባቴ ያቀበለውን ድንቅ ኳስ ዮሴፍ ታረቀኝ አስቆጥሮ ኢትዮጵያን አቻ አድርጓል።

ጨዋታው ከዕረፍት ተመልሶ አራት ደቂቃዎች እንዳለፉ ከቅጣት ምት በተነሳ እና አቱማኒ ማካንቦ በግንባሩ ባስቆጠረው ኳስ ታንዛኒያ በድጋሚ መምራት ችላለች። ቡድኑ መሪነቱን የሚያሰፋበት የፍፁም ቅጣት ምት ዕድል አግኝቶም ሳይጠቀም ቀርቷል። ከዚህ ውጪ 80ኛው ደቂቃ ላይ የታንዛኒያው ግብ ጠባቂ ባስተናገደው ጉዳት ከአራት ደቂቃ በላይ የሕክምና ዕርዳታ ሲደረግለት ቆይቷል። በዚህ ክስተት ምክንያት ሰባት ያህል ተጨማሪ ደቂቃዎች በተስተናገዱበት ጨዋታ 87ኛው ደቂቃ ላይ ከተጠባባቂ ወንበር የተነሳው ከድር ዓሊ ኢትዮጵያን አቻ የምታደርግ ወሳኝ ጎል አስቆጥሯል። ጨዋታው በጭማሪዎቹ ደቂቃዎች ሌላ ግብ ሳያስተናግድም 2ለ2 ተጠናቋል።

ኢትዮጵያ በምድቡ ሁለተኛ ጨዋታ ከትናንት በስቲያ ዩጋንዳን ገጥማም አንድ ለምንም በሆነ ውጤት ስታጠናቅቅ ብቸዋን ግብ ከድር ዓሊ ከመረብ አሳርፏል። በዚህም ኢትዮጵያ ምድቧን በ4 ነጥብ በቀዳሚነት በማጠናቀቅ ወደ ግማሽ ፍፃሜ ማለፏን አረጋግጣለች።

ኢትዮጵያ በዛሬው እለትም በግማሽ ፍፃሜው ፍልሚያ ደቡብ ሱዳንን የምትገጥም ሲሆን ወደ ፍጻሜ ማለፍ ከቻለች በግብጽ በሚካሄደው ከ20 አመት በታች አፍሪካ ዋንጫ ላይ መሳተፍ የሚያስችላትን ትኬት በእጇ ታስገባለች።

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ምድቡን በበላይነት እንዲያጠናቅቅ ያስቻለውን ድል ዩጋንዳ ላይ ካስመዘገበ በኋላ ባለፉት ሁለት ቀናት ወደ ልምምድ ተመልሶ ለዛሬው ወሳኝ የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታ ዝግጅቱን እንደቀጠለ ከስፍራው የወጡ መረጃዎች ጠቁመዋል።

ሰባት ቡድኖች በሚሳተፉበት የዘንድሮው ከ20 ዓመት በታች የሴካፋ ውድድር ለፍጻሜ የሚቀርቡ ሁለት ቡድኖች በ2023 የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች አፍሪካ ዋንጫ ላይ በቀጥታ ይሳተፋሉ።

በምድብ አንድ አስተናጋጇ ሱዳን ከቡሩንዲ፣ደቡብ ሱዳንና ጅቡቲ ጋር መደልደላቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ሱዳን የግማሽ ፍጻሜው ተፋላሚ ሆናለች። በዚህም ወደ ዋንጫ ፍልሚያው ለማለፍ ከምድብ ሁለት ሁለተኛ ሆና ያለፈችው ዩጋንዳን ትገጥማለች። በምድብ አንድ ሁለተኛ ሆና ግማሽ ፍጻሜውን የተቀላቀለችው ደቡብ ሱዳን ደግሞ ኢትዮጵያን የምትገጥም ሀገር ናት።

የሴካፋ ከ20 ዓመት በታች ውድድር በመካከለኛውና ምሥራቅ አፍሪካ እግር ኳስ ምክር ቤት አማካኝነት ሃያ አባል ሀገራትን ያካተተ አንጋፋ የውድድር መድረክ ሆኖ እኤአ ከ1971 ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል።

ውድድሩ ብዙ ጊዜ በየሁለት ዓመቱ አልፎ አልፎም በሦስትና አራት ዓመት ልዩነት ሲካሄድ ቆይቷል። ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም ከተካሄዱ አስራ ሁለት ውድድሮች በሦስቱ ዋንጫ ማንሳት ችላለች። ይህም እኤአ በ1995 ኬንያ ባስተናገደችው ውድድር በፍጻሜ ጨዋታ ታንዛኒያን በመርታት ለመጀመሪያ ጊዜ ሻምፒዮን የሆነችበት አንዱ ነው። በቀጣይም ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባስተናገደችው ብቸኛ ውድድር እኤአ በ1996 ዩጋንዳን በፍጻሜ ጨዋታ አሸንፋ ያነሳችው ዋንጫ ተጠቃሽ ሲሆን፣ እኤአ 2005 ላይ ዛንዚባር ባስተናገደችው ውድድር ቡሩንዲን በፍጻሜ ጨዋታ አሸንፋ ሻምፒዮን እንደነበረች ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ሦስት ጊዜ ቻምፒዮን በመሆን ስኬታማ ከሚባሉ ሀገራት አንዷ ስትሆን ዩጋንዳ አራት ጊዜ የዋንጫ ባለቤት በመሆን ቀዳሚ ናት።



የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ወደ አፍሪካ ዋንጫ ስማስፍ የ90 ደቂቃ ፍልሚያ ብቻ ቀርቶታል፣


### የብሬክስሩ ትሬዲንግ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ እና የ2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ

የብሬክስሩ ትሬዲንግ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሕዳር 21 ቀን /2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሠዓት በሸራተን አዲስ ሆቴል ላሊበላ የስብሰባ አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን እና ቦታ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርታችሁን በመያዝ በጉባዔው ላይ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርብላችኋል፡፡

የጉባዔው አጀንዳዎች፡-

- **የ2014 የበጀት ዓመት ማጠቃለያ የኦዲተሮችን እና የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት ማዳመጥ እና ውሳኔ ማሳለፍ፣**
- **የጎደሉ ሁለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምትክ እና ተጠባባቂ ሁለት የቦርድ አባላትን መምረጥ፣**
- **የቦርድ አባላትን ውስጠ-ደንብ ማጽደቅ እና የቦርድ አባላትን የሥራ ዋጋ መወሰን፣**
- **የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻል፣**
- **የማኅበሩን መመስረቻ ካፒታል ማሳደግ**

ምልዐተ-ጉባዔው ከተሟላ፣ በዕለቱ በጉባዔው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ ባልተገኙ ባለአክሲዮኖች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ቦርዱ እያሳወቀ፣ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የማትችሉ ባለአክሲዮኖች በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ተቋም የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ በማቅረብ ወይም አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ-ከተማ ወረዳ 03 አለምነሽ ፕላዛ ስድስተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 601 በሚገኘው የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በአካል በመገኘት በተዘጋጀው የውክልና ሰነድ ላይ ከስብሰባው በፊት ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ውክልና መስጠት የምትችሉ መሆኑን የዳይሬክተሮች ቦርድ ያሳውቃል፡፡ በተጨማሪም በጎደሉ ሁለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምትክ እና ተጠባባቂ ሁለት የቦርድ አባላትን ለመምረጥ በእጩነት የሚቀርቡትን ሰዎች ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ ድረስ በመገኘት ጥቆማ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ይገልፃል፡፡

**ብሬክስሩ ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር የዳየሬክተሮች ቦርድ**

### የባለአክስዮኖች 12ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

- ሐሴት የጅምላ ንግድ ቢዝነስ አክስዮን ማኅበር 12ኛውን መደበኛ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቅዳሜ ህዳር 24 ቀን 2015 ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በአምባሳደር ቴአትር ቤት አዳራሽ ያካሂዳል፡፡

ስለሆነም ባለአክስዮኖች ወይም ህጋዊ ተወካዮች በሙሉ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**የ12ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች**

1. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፣
2. የ2014 ዓ.ም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥ፣
3. የ2014 ዓ.ም የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ማድመጥ፣
4. በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ላይ መወያየትና ማፅደቅ፣
5. በ2014 በጀት ዓመት በተገኘ የትርፍ ክፍፍል ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
6. ተተኪ የዳይሬከተሮች ቦርድ አባል ማፀደቅ፣
7. ለቀጣይ 3 ዓመታት የሚያገለግሉ የውጭ ኦዲተሮች መምረጥና የአገልግሎት ክፍያቸውን መወሰን፣
8. የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ማፅደቅ፣

**ማሳሰቢያ:-**

ባለ አክስዮኖች የታደሰ መታወቂያ ካርድ ወይም የባለ አክስዮኖች ህጋዊ ተወካዮች አግባብነት ካለው የመንግስት አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

በስብሰባው ላይ በአካል መገኘት የማትችሉ ባለአክስዮኖች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ኢቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት አካባቢ በሚገኘው ሸገር ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 411 የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በመቅረብ ለዚሁ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ በመሙላት ተወካዮቻችሁን ማሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

ስልክ ቁጥሮች - 0114403879 / 0911-528335/ 0114- 403103 / 0114- 402808

**ሐሴት የጅምላ ንግድ ቢዝነስ አክስዮን ማኅበር**